# ኢትዮጵያ፤ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ፍለጋ

## ለተሐድሶ እና ለሽግግር ዘመን የፍኖተ ካርታ ጥቆማ

ሐምሌ 2010

**በመስፍን ነጋሽ**

ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ ሥልጣን ከያዙ መቶ ቀናት አለፉ። አገራዊ መነቃቃትን የፈጠሩ፣ ተስፋና ስጋትን ያጣመሩ ሳምንታት ናቸው። አጋጣሚውን ልንጠቀምበት ወይም ልናባክነው የምንችለው አንድ አገራዊ ዕድል አድርገው ከሚቆጥሩት ውስጥ ነኝ። በዚህ ደረጃ፣ የሚያስመሰግኑም የሚተቹም ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ ለጊዜው በጣም ወሳኝ በምለው አንድ ቁልፍ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩራለሁ። የዚህ ጽሑፍ የትኩረት አቅጣጫ አገራችን እያለፈችበት ያለውን ፖለቲካዊ ለውጥ በየምኅዳሩና በየተዋናዩ አንጻር ለመረዳት መሞከር እና ለዘላቂ ስኬቱ ቁልፍ ነው ያልኩትን የፍኖተ ካርታ ጉዳይ ማዘከር ነው።

በየዕለቱ የሚሰማው የለውጥ ዜና ብዛትና አይነት አድማጩን በፈጣን የፖለትካ ዜና መንኮራኩር እንደመጓዝ ያለ ስሜትን ውስጥ ከቶታል። ለመዝናኛነት በሚሠራው "የሃዲድ መንኮራኩር" (Roller coaster) የሔደ ሰው እንደሚያውቀው፣ በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን፣ መንኮራኩሩ በማይገመት ፍጥነትና መከረባበት ሲነጉድ ተጓዡ የሚያስበው "ቀጥሎስ ወዴት ይታጠፍ ይሆን? ምን ያህል ሽቅብ ወጥቶ እንደምን ተምዘግዝጎ ሊወርድ ይችላል? መንኮራኩሩ የሚቆመው መቼ ነው?"ን የመሳሰሉ የምጥ ላይ ጥያቄዎችን ብቻ ነው። የመንኩራኩር ተጓዡ ቁልፍ ጥያቄው አንድ ብቻ ነው፤ "መቼ ቆሞ ወርጄ!" አለዚያም "ምነው ይኼ ደስታ ባላለቀ!" በዚህ መንኮራኩር [ለመጀመሪያ ጊዜ] የሚሄድ ሰው፣ ከምጥ ላይ ጥያቄዎቹ ተፋቶ ስለመንኮራኩሩ መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን (ሠሪና አሠራሩን፣ ስለንድፉና ቴክኒካዊ ውጥንቅጡ፣ ስለፍጥነቱና ስለርዝመቱ፣ ስለመቆጣጠሪያውና መዳራሻው ወዘተ) የሚያስብበት ጊዜም ቀልብም የለውም። በነጠላ ድርጊቶችና በዜናዎች መንኮራኩር ውስጥ ገብተን እየተናጥን ነው ወይስ [ቢያንስ እገረ መንገድ] መሠረታዊ ጥያቄዎችን እየመለስን በፍጥነት እየተጓዝን ነው?

ለመሆኑ አሁን እየተካሔደ ያለው ለውጥ ቁልፍ ተዋንያን እነማን ናቸው? ተዋንያኑና ለውጡ እየተካሔደ ያለው በየትኞቹ ምኅዳሮች ላይ ነው? ሒደቱን አስቀድመን ለመገመት የሚያስችለ(ሉ)ን ፍኖተ ካርታ(ዎች) አዘጋጅተናል ወይም እያዘጋጀን ነውን? ዘርዘር ያለ ሒደትን የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ መኖር እንዳለበት ለመጠቆም የሞከርኩት ጠ/ሚ ዐቢይ ወደ ሥልጣን እንደመጡ ሰሞን ነበር።[1] ጥያቄው የእኔ ብቻም አልነበረም፤ አይደለም። አሁን ላይ ሆኜ ሳየው፣ የዕለት ዜናዎችን በመከታተልና ትርጉማቸውን ለመረዳት በመሞከር ተጠምደናል። እየተወሰዱ ያሉትን እርምጃዎች፣ እየታዩ ያሉትን ለውጦች እግር በግር እየተከታተሉ ማሔሱ መልካም ነው። ቢሆንም አማራጭ ፍኖተ ካርታዎች እየቀረቡ መነጋገር ካልቻልን የነጠላ ሁነቶቹን ክብደትና ውጤት በአግባቡ መመዘን አንችልም። አሁን የተፈጠረው የለውጥ መንፈስ የሚገባውን ያህል ሳንጠቀምበት ሊቀዛቀዝ፣ ዜና በመከታተል ጉልበታችንን ልንጨርስ፣ ምናልባትም የለውጡ መንፈስ ሊቀለበስ ይችላል። ይህ ሁኔታ፣ እንዲሁም የጥቂት ወዳጆቼ ጉትጎታ፣ ሌሎችን ከማሳሰብና ከማስታወስ አልፎ የበኩሌን ሐሳብ እንዳዋጣ አስገድዶኛል። በዚህ ሙከራዬ አንኳር ያልኳቸውን ጉዳዮች በማንሣት ውይይት ለመጋበዝ እሞክራለሁ።[2] ምናልባት ከተሳካልኝ፣ አማራጭ ፍኖተ ካርታዎች ወደ አደባባይ እንዲመጡ ለማነቃቃት እሞክራለሁ። ሙከራ ነው።

ይህ ሙከራ በዋናነት የሚመለከተው የፖለቲካውን ምህዋር እንደሆነ ማስታወስ እወዳለሁ። ከፖለቲካዊ ለውጦች ጋራ ተያይዞ በተለይም የኢኮኖሚው ዘርፍ ተመሳሳይ ፍኖተ ካርታ ሊበጅላቸው ይገባል። የሽግግር ፖለቲካን ከወቅቱ

---

[1] ለምሳሌ ጠ/ሚሩ የካቢኔ አባሎቻቸውን ባስታወቁበት ሰሞን የአሜርካ ድምጽ ሬዲዮ (ቪኦኤ) የአማርኛ ክፍል ባስተናገደው ውይይት ላይ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት እንደሚኖርባቸው አስረግጬ ተከራክሬ ነበር፤ በተለይ በሁለተኛው የውይይቱ ክፍል። (https://amharic.voanews.com/a/ethiopia-new-pm-cabinet-new-era-tsedale-lemma-mesfin-negash-henok-with-voa-alula-kebede-april-2018/4365419.html )

[2] ይህ ጽሑፍ ከሆነው በላይ እንዳይረዝም እና ሐሳቦቹም በነጠላው ቢቀርቡ የሚከብዱ ባለመሆናቸው ምሳሌዎችን ከመዘርዘር ተቆጥቤያለሁ። ከዚህም በላይ ግን ሌሎች አገሮችን ወደ "መኮረጅ ፈተና" (temptation of imitation) እንዳንወደቅ፣ ፈተናውን ለማራቅም ጭምር የሌሎች አገሮችን ምሳሌ ላለማንሣት እሞክራለሁ።

ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ነጥሎ ማየት አስቸጋሪ ነው። እንዲያውም፣ የሽግግር ፖለቲካና ኢኮኖሚ አንዳቸው የሌላቸው እስረኞች ናቸው ማለት ይቻላል። እንዲዚያም ቢሆን፣ የኢኮኖሚው ጉዳይ በተለየ መጣጥፍና መድረክ ለብቻው ሊዳሰስ እንደሚገባው በማመምን፣ እንዲሁም ጉዳዩን ከእኔ በተሻለ የሚያውቁት ሰዎች ቢጀምሩት ይሻላል ከሚል እምነት በዚህ ጽሑፍ እንዳለ ማለፉን መርጫለሁ። የሚከተሉትን መሞች ተከትዬ ሐሳቤን ለማስተንተን እሞክራለሁ።

ሀ፤ በእንተ ፍኖተ ካርታ(ዎች)፤ መተማመን ብቻ አይበቃም ለወዳጅ!
ለ፤ የለውጡ ሒደት ተፋሰስ፤ ተዋንያኑ በየምኅዳራቸው
ሐ፤ የሰማናቸው ወሳኝ መዳረሻዎች፣ እንደ ፍኖተ ካርታ ውስዋስ
መ፤ አንኳር የለውጡን ባህርያት ፍለጋ

## 1፤ መተማመን ብቻ አይበቃም! ለወዳጅ

በአገራችን አትኩሮት የሚስብ፣ በጉጉትና በስጋት የሚወጥር፣ ችላ የማይሉት የለውጥ ነፋስ እየነፈስ ነው።[3] በብዙ መልኩ አገሪቱ ከወሳኝ የታሪክ መታጠፊያ ላይ ደርሳለች። ወሳኝ የታሪክ መታጠፊያዎች[4] ባሉበት መቆየትን አይፈቅዱም፤ ወደፊት መራመድ ወይም ወደኋላ መንሸራተት የማይቀር ፍጻሜ ነው። ያሁኑ ለውጥ እርግጠኛ አቅጣጫውም ሆነ መዳረሻው ለማንም ግልጽና የማያሻማ ሆኖ አይታይም። የለውጡን ትክክለኛ ፍጥነት መገመት አይቻልም። ምናልባት የለውጡን ይዘትና መዳራሻ ከሌላው በተሻለ ሊገምቱ የሚችሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እና ቡድናቸው ናቸው። በኢሕአዴግ ደረጃ ይህን መሰሉን ፍኖተ ካርታ ለማውጣት የሚያስችል ውስጣዊ መግባባትና ጤንነት ያለ አይመስለም። ለውጡን በተለያዩ ምክንያቶች የሚቃወሙ ቡድኖችም በየፊናቸው የየራሳቸውን ትልም እያሰመሩ መሆኑ ግልጽ ነው። ሌላው ሕዝብ የራሱን ተስፋ ከለውጡ ባህር ውስጥ ለማጥመድ የወጣ አስጋሪ ነው። ዓሳውን ሊያገኘውም ሊያጣውም ይችላል፤ ምናልባትም የሚፈልገው ዓሳ እዚህ ባህር ውስጥ አይገኝ ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ (ጠ/ሚሩ) ሥልጣን ከያዙ ጀምሮ በርካታ ተስፋ ሰጪ እርምጃዎችን እየወሰዱ ነው። በየዕለቱ የሚደረጉ ነጠላ እርምጃዎች አገሪቱ በሆነ አይነት የለውጥ ሒደት ውስጥ እያለፈች መሆኑን በማያጠራጥር መልኩ ይናገራሉ። ይሁንና እነዚህ ነጠላ ለውጦችና ክስተቶች በራሳቸው ካላቸው ትርጉምና ክብደት አልፎ በአጠቃላዩ ሒደት ውስጥ ያላቸውን ስፍራ በምልአት ለመረዳት አይቻልም፤ መገመት እና መመኘት እንጂ። ነጠላዎቹ ክስተቶች በምን እና እንዴት እንደሚያያዙ፣ ተደጋግፈውም ይሁን ተቃርነው ወደየትኛው የለውጥ ወንዝ እንዲፈሱ እንደታቀደ፤ ይህ ሒደት ምን ያህል ዋጋ እና ጊዜ እንደሚፈልግ፤ የትኞቹ አካሎች መቼና እንዴት የሒደቱ ባለቤቶችና ተስታፊዎች እንደሚሆኑ ወዘተ ማስረዳት ቀርቶ ሊጠቁሙን የሚሞክሩ ዝርዝር ፍኖተ ካርታዎች የሉም። በነጠላ ክስተቶቹ ከመደመም፣ ከመደነቅ፣ ከመደንገጥ፣ ምናልባት ከማዘን አልፎ የለውጡን ጎርፍ ምንነት በቅጡ ለመረዳት ገና ትግል ላይ ነን።

ከአራት ወራት በፊት የነበረው የፖለቲካ ድባብ፣ ለ27 ዓመታት ከዘለቀው እጅግ አሳፋሪ አፈናና የአመራር ልሽቀት ጋር ተደምሮ አሁን የሚታዩትን ለውጦች በትክክለኛ ዋጋቸው እንዳንመዝናቸው ሊያደርገን እንደሚችል እጠረጥራለሁ። ከዚያ ባስ ሲል ደግሞ፣ የለውጥ ተስፋው በይዘቱ፣ በቅርጹ፣ በመንገዱና በውጤቱ ምን ሊመስል እንደሚችል የሚጠቁም ፍኖተ ካርታ እና አማራጮቹ አለመኖር ሒደቱን በበለጠ ጥንቃቄ እንድንመለከተው የሚያስገድድ ነው። ሒደቱን የሚደግፉም ሆኑ በተለያየ ምክንያት የሚጠረጥሩ ወገኖች፣ ሒደቱን በተሻለ መልኩ የሚረዱበትና የሚተነትኑበትን፣ የየቡድኖቹን ምኞትና ግብ የሚያሳዩ ፍኖተ ካርታዎች በሌሉበት፣ አትኩሮታችን በቅንጭብ ጥያቄዎችና ምኞቶች ተጠልፎ እንዳይቀር እየሰጋሁ ነው። አሁን ያለው የለውጥ መንፈስና ጅምርም ይሁን ነጠላ ድርጊቶች ሊቀለበሱ፣ ሊከሽፉ ወይም ሊጠለፉ እንደሚችሉ ማስታወስ አስፈላጊ ነው።[5] ነጠላ ድርጊቶችን/እርምጃዎችን መደገፍ አጠቃላይ ሒደትን ከመረዳትና

---

[3] ወቅቱ በየዕለቱ በርካታ ኹነቶች የሚከሰቱበትና የሚዘገቡበት ነው። በዚህም የተነሣ እዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱ ምሳሌዎችን እና አንዳንድ ክርክሮችን በመከለስ ወቅቱን እንዲያንጸባርቁ ሞክሬያለሁ። ሆኖም በኹነቶች ፍጥነት ልክ መከተል የሚቻል አይደለም። ኹነቶቹ በአብዛኛው ይህ ጽሑፍ የሚያጠነጥንባቸውን አንኳር ጉዳዮች በመሠረቱ የሚመልሱ ወይም አላስፈላጊ የሚያደርጉ እንደማይሆኑ ተስፋዬ ነው። ከሆነም፣ ስጋቶቼ ተመልሰዋል ማለት ነውና የሚያስከፋ አይሆንም።

[4] "A critical juncture is a doube-edged sword that can cause a sharp turn in the trajectory of a nation." Daron Acemoglu and James A. Robinson in 'Why Nations Fail: The Origins of Power, Proseperity and Poverty.'

[5] በቅርቡ Historical photos from the Horn of Africa በተባለ የፌስቡክ ገጽ ላይ "The Ethiopian revolution and The Peasants 1975" በሚል ርእስ ጁን 9 ቀን 2018 በ18:56 የተሰራጨ የአንድ እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ ሪፖርት ተመልክቼ ነበር። ዘገባው በዋናነት አብዮቱ ያመጣውን የመሬት ባለቤትነት አዋጁ የፈጠረውን ስሜትና ለውጥ ይዳስሳል። ጋዜጠኛው ካናገራቸው ሁለት የመሬት ይዞታ ማሻሻያ እና የግብርና ሚኒስቴር ሐላፊዎች አንዱ ስለ መሬት ይዞታ ለውጡ በዚያውም ስለሕዝቡ ስሜት እንዲህ ይላል። "...It can't possibly go wrong with all this excitement and participation

ከመደገፍ በእጅጉ የተለየ ነው። ምክንያቱም በአጠቃላይ ሒደቱና በታሰበው ግብ ላይ የተስማማ ወገን፣ በነጠላ ድርጊቶች ባይስማማ እንኳን ትችቱን እያቀረበ ለሒደቱ ታማኝ ደጋፊ ሆኖ ይቀጥላል። በነጠላ እርምጃዎች ላይ የተመሠረተ አጋርነት ጊዜያዊ ከመሆን አያልፍም፤ ይህ አይነቱ ደጋፊ የማይስማማበት ነጠላ እርምጃ ሲወሰድ (አውቆም ይሁን ሳያውቀው) የአጠቃላይ ሒደቱ ተቃዋሚ ሊሆን ይችላል። እርግጥ ድጋፉ የፋሽን፣ ጥርጣሬው የልማድ ጉዳይ የሚሆንበት አይጠፋ ይሆናል። ያም ሆነ ይህ፣ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ማግኘት ብቻውን ለለውጡ ስኬትና ዘላቂነት ማረጋገጫ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም።[6]

የዐቢይ አህመድ አስተዳደር እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች ምንም ያልታሰበባቸውና የአጋጣሚ እንዳልሆኑ መገመት አያስቸግርም። ዐቢይና ቡድኑ የሚሠሩትን ያውቃሉ።[7] በጅምሮቻቸው ተስፋና መነቃቃት ፈጥረዋል። ዜጎችን በሒደቱ ላይ መተማመን እንዲችሉ፣ ባለቤትና ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ መረጃ ያላቸው ተቿዎች እንዲወጣቸው ግን የተጀመረውን ለውጥ አጠቃላይ ስዕል የሚያሳይ፣ ሒደቱን የሚተነበይ የሚያደርግ ፍኖተ ካርታ ማቅረብ ያስፈልጋል። ውይይት የሚደረግበት፣ ትችት የሚሰነዘርበት ፍኖተ ካርታ በሌለበት የአገራዊ ሽግግር ተስፋ በነጠላ እርምጃዎች እርካታ ሊሸፈን ይችላል። በተጨማሪም፣ ሌሎች ወገኖች የየራሳቸውን አማራጭ ፍኖተ ካርታዎች እንዲያቀርቡ አያነሣሣም፤ ይህም ለአገራችን ጠቃሚ አይደለም።

ፍኖተ ካርታውን ማዘጋጀትና መግለጥ ሕዝቡና የተለያዩ ቡድኖች ሒደቱን በትክክል ተረድተው በሙሉ ልብ እንዲደግፉትና ከቅልበሳ እንዲጠብቁት፣ ከሒደቱ ምንና መቼ እንደሚገኝ እንዲያውቁ፣ በየትኞቹ አካባቢዎች ምን አይነት ግፊትና ተሳትፎ ማድረግ እንደሚገባቸው እንዲረዱ ወዘተ ያደርጋል። ይህም ሒደቱን የጠ/ሚሩ ቡድን ብቻ ሳይሆን ሕዝብና ከመንግሥት ውጭ ያሉ ቡድኖችም የእኔ ብለው እንዲደግፉት ወይም እንዲተቹት ያበረታታል። ነጠላ ድርጊቶችን/እርምጃዎችን መደገፍ አጠቃላይ ሒደትን ከመረዳትና ከመደገፍ በእጅጉ የተለየ መሆኑን አስቀድሜ ጠቆም አድርጌያለሁ።

አዲሱ ጠ/ሚ በየንግግሮቻቸው ከገለጿቸው ፍላጎትና አቅጣጫ-ጠቋሚ ብልጭታዎች፣ እንዲሁም እየወሰዷቸው ካሉ እጅግ ጠቃሚ እርምጃዎች ውጭ አጠቃላይ እቅዳቸውን የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ ያላቀረቡባቸው ምክንያቶች ይኖራሉ። አንደኛው ምክንያት ፍኖተ ካርታው ተዘጋጅቶ ወይም በዝግጅት ላይ ሆኖ፣ ሒደቱን ለማደናቀፍ ወይም ለመቀልበስ ለሚፈልጉ (ውስጣዊና ውጫዊ ቡድኖች) የማይገባ የመዘጋጃ እድል ይሰጣቸዋል በሚል ስጋት ተደብቆ ሊሆን ይችላል። ስጋቱ በተወሰን መልኩ ተገቢነት ቢኖረውም፣ በምሥጢር መጠበቅ የሚገባቸውን ለይቶ በመያዝ አደጋውን መቀነስ ይቻላል። አሁን ባለንበት፣ ፍኖተ ካርታው ስለመኖሩም በእርግጠኝነት የምናውቀው ነገር የለም።

ሁለተኛው ግምቴ፣ የጠ/ሚ ዐቢይ አስተዳደር ወደሥልጣን ከመጣበት እጅግ የተፋጠነና ፍትጊያ የበዛበት ሒደት አንጻር፣ የተሟላ ፍኖተ ካርታ ለማዘጋጀት የሚያስችል በቂ ጊዜና ምቹ ሁኔታ አላገኘ ይሆናል። በዚህም የተነሣ፣ ፎኖተ ካርታ ከማዘጋጀት ይልቅ በቀጥታ አስቀድሞ በግልጽ የሚታወቁ የተበላሹ አሠራሮችንና ተቋማትን ወደማስተካከል መግባት ተመርጦ ሊሆን ይችላል። ይህ አካሔድ በተለይ ኢሕአዴግ ውስጥ ካለው አደገኛ ፍትጊያ አንጻር በመጀመሪያዎቹ ወራት አማራጭ የሌለው ነበር ብሎ መከራከር ይቻላል። ይህ መከራከሪያ ግን  ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል አይደለም። በእኔ ግምት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ መስከረም 30 ቀን 2011 ዓ ም ፍኖተ ካርታቸውን ለሕዝብ ማቅረብ አለባቸው።[8] ብዙ ጊዜ የለም።

ሦስተኛው ግምት፣ ጠ/ሚሩ “ጥገናዊ ለውጥ” ከማድረግ ያለፈ አጀንዳ የላቸውም፤ ስለዚህም እጅግ አፋኝ የሆኑ አሠራሮችን ከማለዘብና ሥርዓቱን እንዳለ ከማስቀጠል የዘለለ አጠቃላይ ለውጥ የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት

---

by the people. After all the revolution is by the people for the people.” አሁን ላይ ሆነን ሰውየው የገለጸው የእርግጠኝነት መጠን በወቅቱ ስሜት ተወስዶ የተናገረው እንደነበር መረዳት አይከብደንም። የአሁኑ የአገራችን የለውጥ መንፈስም እንዲሁ በጭራሽ ሊቀለበስ ወይም ሊከሽፍ የማችል እንዳይመስለን የሚያስታውስ ታሪካዊ አጋጣሚ ይመስለኛል። (https://www.facebook.com/groups/101239070216241/permalink/662443397429136/)

[6] የታሪክን የፖለቲካ ምሁሩ ሆብስባውም “…history is a useful warning against confusing fashion with progress” ይላል፤ “On History” በተባለው መጽሐፉ።

[7] ይሁንና፣ ይህ እነርሱ በግልጽ የተረዱትና በስልት እየተገበሩት የሚመስለን ሒደት ሌላው ቀርቶ ወደራሳቸው ፓርቲ (ኢሕአዴግ) እና ወደ መንግሥት ተቋማት “እንዲጋባ” ለማድረግ የሚያስችል የተቀመረ የውስጥ እቅድ መኖሩን እርግጠኞች አይደለንም። ይህን ቀመር ለማዘጋጀት ጊዜ ሊያጥር እንደሚችል እገነዘባለሁ። ለጊዜው ጥያቄዬ፣ ዝግጅቱ ተጀምሯል ወይ የሚል ነው።

[8] መስከረም 30ን የመረጥኩበት ምክንያት ጠ/ሚሩ ወደሥልጣን ከመጡ ስድስት ወር ስለሚሞላቸው ነው። ቀኑ ሊቀየር ይችላል፤ ብዙ መራቅ ግን የለበትም ብዬ አምናለሁ።

አይፈልጉም (አይችሉም) የሚል ነው። እስካሁን ከሰማናቸው ንግግሮችና ካየናቸው ጅምር እርምጃዎች ተነስቼ ሳየው፣ ይህንን ግምት በዚህ ሰዓት ለመቀበል እቸገራለሁ።

አራተኛው ግምት፣ ከኢሕአዴግ ከራሱ ውስጣዊ የድርጅት ጤና መታወክ በሚመነጭ ምክን ያት ነው። ኢሕአዴግ ውስጥ የሚታየው ውስጣዊ ሽኩቻ የተጀመረውን ለውጥ እስከመቃወም የሚያደርስ መሆኑ በአደባባይ የሚታይ ነው። አቅልጦና ቀጥቅጦ የሚመራ ሊቀ መንበር የለመደው ግንባር፣ እንደ ኃይለ ማርማይ ደሳለኝ ለንቋሳ፣ እንደ ዐቢይ አህመድ አዲስ ሰው ለመልመድ ጊዜ ቢፈጅበት የሚጠበቅ ነው። ችግሩ ከዚያ የዘለለ እንደሆነ ግልጽ ነው። ዐቢይ አህመድ በኢሕአዴግ ደረጃ የሽግግር አጀንዳውን ተቀባይ አድርጎ፣ በአንድ በኩል ግንባሩን ራሱን፣ በሌላ በኩል የአገሪቱን መንግሥትና ሥርዓት የሚያሻሽሉ ፎኖተ ካርታዎችን ማዘጋጀትና ማጸደቅ አስቸጋሪ እንደሚሆነበት መገመት አይከብድም። ትልቁ የመሪነት ፈተናውም ያለው እዚህ ላይ ነው። ሌሎች እኔ ከቆምኩበት የማይታዩ ምክንያቶችም ይኖሩ ይሆናል።

አዲሱ ጠ/ሚ እና መስተዳድራቸው በቂ ክብደት ያልሰጡት የሚመስለኝ አንዱ ጉዳይ፣ የሕዝቡ የለውጥ ፍላጎት እና እየገነባው ያለው ተስፋ፣ ለአዲሱ መሪ አቅም ብቻ ሳይሆን እዳ የመሆኑን እውነታ ነው። እንደምታዘበው ከሆነ የሕዝቡ ተስፋ እና ጥበቃ እጅግ የተጋነነ እየሆነ ነው። ይህ ተስፋና ጥበቃ ሳይረፍድ በየአቅጣጫው ልጓም ሊበጅለት ይገባል። ከእነዚህ ልጓሞች አንዱ ብዙዎች የሚስማሙበት፣ ባይስማሙበትም የሚያውቁት፣ አገራዊ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ነው። ሁሉም በየፊናው ሕልም ከቅዠት እየቀላቀለ፣ የሚቻለውን ከማይቻለው እያደባለቀ፣ አስቸኳዩን ከሚያሳድረው እየበወዘ የሚነጉድ ከሆነ እንኳን መግባባት መደማመጥም አስቸጋሪ ይሆናል። ፍኖተ ካርታ ማቅረብ የተለያዩ ወገኖች ተስፋና ጥበቃቸውን በልክ እንዲያደርጉ የሚያነቃ ደውል ይሆናል።

አገራዊ ተሐድሶ እና ሽግግር ከአንድ በላይ አማራጭ ፍኖተ ካርታዎች ቢኖሩት የሚመረጥ ነው። ፍኖተ ካርታ የማቅረቡ ኀላፊነት የኢሕአዴግ እና የመንግሥት ብቻ ሊሆን እንደማይችልና እንደሌለበትም የታመነበት ነው። ከዚህ አንጻር ተቃዋሚዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ እና ሌሎችም ስብስቦች የየራሳቸውን አማራጭ ፍኖተ ካርታዎች በማቅረብ በለውጥ ሒደቱ አጀንዳ ላይ ቢያንስ ተጽዕኖ ለመፍጠር ይጠቀሙበታል የሚል ተስፋ ነበረኝ። እያንዳንዳቸው አገራዊ ፍኖተ ካርታ ሊያቀርቡ ባይችሉ እንኳን የየራሳቸው ዘርፍ ስለሽግግሩ የሚታየውንና ሊያበረክት የሚችለውን ቀምሮ ማቅረብ ያስፈልጋል። ምናልባት ሳላየው ቀርቼ ካልሆነ በቀር ዘርዘር ያለ አገራዊም ይሁን ዘርፍ ተኮር ትንተናና አቅጣጫ የሰጠ አካል አላየሁም።[9] ለምሳሌ፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ ለሽግግሩ ግብአት ሊሆኑ የሚችሉ ሐሳቦችን ማቅረብ አይችልም? አገራዊ ምሳሌ ለመስጠት፣ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያዎችና ጠበቆች ስለሕግ ሥርዐት ማሻሻያው የራሳቸውን የቢሆን ፍኖተ ካርታ አዘጋጅተው ማቅረብ የማይችሉበት ምክንያት አይገባኝም። እርሱን ይዞ አሁን የተቋቋመውን ምክር ቤት መወትወትና መመዘን ይቻላል። አለበለዚያ ግን ምክር ቤቱ ጨርሶ ባመጣው ጉዳይ ላይ በሚጠራ ስብሰባ ላይ ተገኝተው የሚንጨረጨሩ የሕግ ባለሞያዎችን ለማየት መጠባበቅ ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት በግለሰቦችም ይሁን በተደራጁ ቡድኖች ለየዘርፉ ቀርበው የነበሩ ሐሳቦች የተረሱ ይመስላሉ፣ አሁን ያለውን ሁኔታ የሚያንጸባርቁ መሆናቸውም አጠራርጣሪ ነው።

ተቃዋሚዎች ቢበዛ መንግሥት ለድርድር እንዲጠራቸው እየጠየቁ ነው፣ ወይም የሽግግር (የአንድነት) መንግሥት እንዲቋቋም እየተጣሩ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ እንቁላሎቻቸውን ሰብስበው ምርጫ በሚባል ቅርጫት ውስጥ ለማስቀመጥ እየተዘጋጁ ነው። ሆኖም ተቃዋሚዎቹ ሌላው ቀርቶ የሚጠይቁት ነገር ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን ዝርዝር ሒደት የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ ገና አላቀረቡም። ይሁነኝ ተብሎ እንዲዳከሙ ሲደረግ በመስንበቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችንም ሆነ የሲቪል ማኅበራቱን ብዙ ልንወቅሳቸው አይገባ ይሆናል፤ እድሉን እንዲጠቀሙበት ማነቃቃት ግን ያስፈልጋል። ። አሁንም ቢሆን ሲቪል ማኅበረሰቡ በጋራም ሆነ በአነስተኛ ዘርፎች ተደራጅቶ በሚገባ የተቀመረ የሽግግር ዘመን ፍላጎቱን የሚያንጸባርቁ ፍኖተ ካርታዎችን አለዚያም ግብአቶችን አዘጋጅቶ መጠበቅ እንዳለበት ይሰማኛል።[10] አብዛኞቹ ግን ሕጎች እስኪሻሻሉ፣ ገለልተኛ ተቋማት እስከሚጠናከሩ ከመጠበቅ ይልቅ አስቀድሞ መዘጋጀት የሚባለውን ከባድ ሥራ መጀመር እንደሚቻል የረሱት ይመስላሉ። እዚህ ነን።

ፍኖተ ካርታ ሲባል፣ እንደ ጉዳዩ ስፋቱና ጥልቀቱ ሊለያይ ይችላል። የማይቀረው ነገር አንድን ዓላማ ለማሳካት የሚቻልበትን መንገድና እቅድ የሚያቀርብ መሆኑ ነው። ከዚህ አኳያ አገራዊ ፍኖተ ካርታ ማቅረብ መንግሥታዊ አቅም

---

[9] በዚህ በኩል ምናልባት ሊጠቀስ የሚችለው እጅግ ቀደም ብሎ “መድረክ” ይባል የነበረው ስብስብ አውጥቶት የነበረው የመደራደሪያ አጀንዳዎች ዝርዝር እና የአርበኞች ግንቦት 7ቱ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) በቅርቡ በዋሽንግተን ዲ ሲ እና በዳላስ ከተሞች ያቀረቧቸው ዘለግ ያሉ የሁኔታ ተንተናዎች ናቸው። ሆኖም እነዚህም ቢሆኑ በተሟላ መልኩ የቀረቡ፣ ሒደትና ውጤትን የሚያስዩ ፍኖተ ካርታዎች አይደሉም። ግፋ ቢል ለአጀንዳ ቀረጻ የሚያገለግሉ ግብአቶች ናቸው።
[10] ሲቪል ማኅበረሰቡ በከፍተኛ ጫና ስር መክረሙና ደካማ መሆኑ ቢታወቅም አስተዋጽዖ ከማድረግ የሚያግድ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም። በቱኒዚያ የቅርብ የዴሞክራሲ ሽግግር ተሞክሮ ከአፈና የወጣው ሲቪል ማኅበረሰብ የተጫወተው ሚና አነቃቂ ምሳሌ ሳይሆን አይቀርም።

ይጠይቃል ይባል ይሆናል። በሽግግር ወቅት ለዘርፍ እና ንዑስ ዘርፎች አማራጭ ፍኖተ ካርታዎችን ማቅረብ ግን የዘርፉ ጉዳይ ጉዳዬ ነው ከሚል የተደራጀ አካል ሁሉ የሚጠበቅ ነው። ፍኖተ ካርታ የማዘጋጀትን ጉዳይ እጅግ ውስብስብና ከባድ አድርጎ ማሰብ አይገባም። ቁም ነገሩ የታሰበበትና በጽሑፍ የሰፈረ አማራጭ አቅጣጫ ጠቋሚ ሰነድ ማዘጋጀት ነው።

የፍኖተ ካርታ ያለህ! የሚለውን ጥሪ "ፍኖተ ካርታችሁን ወዲህ በሉ!" ብሎ መደምደም ይቻል ነበር። ምናልባትም የፍቅር ቋንቋ ለሚመርጥ እንዲህ፤

*ፈርማና ወረቀት ቢሆንም ተቀዳጅ ፣*
*መተማመን ብቻ አይበቃም! ለወዳጅ!*

## 2፤ የለውጡ ሒደት ተፋሰስ በየምኅዳሩ

በጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ ወደ ሥልጣን መምጣት የበለጠ የተነቃቃው የለውጥ ተስፋ ቀጣይ እርምጃ ምን መሆን እንዳለበት ወይም እንደሚችል የሚሰጡ በርከት ያሉ አስተያየቶች አሉ። ንፋሱ የሚነፍስበትን አቅጣጫና ፍጥነቱን ማወቅ ለመርከበኛውም ይሁን ለተሳፋሪው ሳይጠቅም አይቀርም። ለመሆኑ የምንፈልገው ለውጥ ሊጀመር የሚገባው ወይም የሚ(ተ)ጀምረው በየትኛው አካልና ፖለቲካዊ ምኅዳር ነው? የምንፈልገው ለውጥ በምን ቅርጽና ቅደመ ተከተል የሚመጣውን ነው?

አገሮች እውነተኛ የዴሞክራሲ ሽግግራቸውን የሚጀምሩ የተለያዩ ተዋንያን ይኖራቸዋል። የእነዚህን የለውጥ ጀማሪዎች እና ተሳታፊዎች ማንነትና ቁመና የሚወስኑት ታሪካዊ ሁኔታዎች ናቸው። ወደዝርዝሩ ሳንገባ፣ ብልህነት፣ ጥረት እና ዕድል የሚፈልገው ቁም ነገር ታሪክ የፈጠረውን አጋጣሚ እጅግ አነስተኛ ዋጋ በሚያስከፍል መንገድ መጠቀም ነው። የለውጡን ምኅዳርና አነሳሽ አካላት ለይቶ ማወቅ ለውይይት ብቻ ሳይሆን ለለውጡ ሊደረግ የሚገባውን ድጋፍም አንጥሮ ለማውጣት ያግዛል።


አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ በአነስተኛ ዋጋ ልናካሒድ የምንችለው ለውጥ በቅደም ተከተል ውጫዊ ግፊት፣ የኢሕአዴግ ተሐድሶ (Reform)፣ አገራዊ ተሐድሶ፣ አገራዊ ሽግግር (Transition)፣ እና አገራዊ የዴሞክራሲ ግንባታ (Consolidation) ሙከራ ነው እላለሁ። በአነስተኛ ዋጋ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ለማድረግ እጅግ ቀናው መንገድ ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ/ቡድን ውስጣዊ ተሐድሶ (ሪፎርም) በማድረግ የለውጡ አካል የሚሆንበት መንገድ ነው።[11] ይህም ገዢውን ፓርቲ የለውጡ አንድ ማዕከል/ምኅዳር እና ወሳኝ ተዋናይ ያደርገዋል፤ የመንግሥት መፍረስ አደጋን በእጅጉ ይቀንሳል። እኛ አገር እየሆነ ያለውም ይኸው ነው፤ ከዘለቀ። አሁን ባለው ሁኔታ ኢሕአዴግ ከነውስጣዊ ቀውሱ አንዱ ቁልፍ ተዋናይ፤ የድርጅቱ ውስጣዊ መስተጋብር የለውጡ አንድ ወሳኝ ምኅዳር ነው። ውስብስቡን አቅልሎ ለማቅረብ ያህል፣ የለውጥ ሒደቱን ተነባባሪ ምኅዳሮች በምስሉ ለማሳየት ተሞክሯል።[12]

በምስሉ ለማሳየት እንደሞከርኩት ከሆነ፣ አገራችን የጀመረችው የተሐድሶ እንቅስቃሴ፣ ከጅምሩ እስከ ስኬታማ ፍጻሜው አምስት ድርብርብ ምኅዳሮች ይኖሩታል። የመቀልበስ አደጋ በሁሉም ምኅዳሮች ቢኖርም በአሁኑ ሁኔታ በጣም ቅርቡና ድርሱ አደጋ ያለው በኢሕአዴግ/መንግሥት (2) እና በአገራዊ ተሐድሶው(3) ምኅዳሮች ውስጥ ነው።

---

[11] በሽግግር ሞዴሎች ላይ ሰፋ ያለ ውይይት የሚሻ ቢኖር በተለይ Transition through extrication, Transition through transaction, Transition after regime breakdown በሚባሉት ጽንሰ ሐሳቦች ላይ መቆዘም ነው።

[12] ይህ ምስል የሚወክላቸው ምኅዳሮች እንደፍላጎታችን በተለያየ መንገድ ሊዋቀር ይችላል። አሁን በቀረበበት መልኩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማኅበራት፣ የተደራጁና ያለተደራጁ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች፣ መገናኛ ብዙኀን ወዘት ከሁለተኛው በስተቀር በሁሉ ምኅዳሮች ውስጥ በተዋናይነት ሊገኙ እንዲሚችሉ፣ እንደሚገባም ታሳቢ ተደርጓል። ሁሉንም ምስሉ ውስጥ ማካተት ምስሉን ስለሚያጣብበው የተተወ ነው።




*ምስል፤ የለውጡ ሒደት ምኅዳሮች ከወሳኝ ጭብጣቸው ጋራ*

- **ምኅዳር አንድ፤ አገራዊ ግፊት እና ቀውስ**

የሕዝብ ግፊት፣ እንዲሁም መነሻቸው ወይም መድረሻቸው የነበሩ ቀውሶች የዛሬው የተሐድሶ ንቅናቄ መሠረቶች መሆናቸው ይታወቃል። የሕዝቡ ግፊት በተለያየ መንገድ ሲካሔድ የሰነበተ፣ እጅግ በርካታ ተዋንያን የተሳተፉበት ነው። ምናልባት በቅርቡ የሆኑትንና ትልልቆቹን እየመረጡ ስም መጥራት ቢቻልም፣ ለውጡን ለአንድ ወይም ለጥቂት አካላት መስጠት የማኅበራዊ ለውጥ ሒደቶችን ውስብስብነት አቃሎ መመልከት አለዚያም የታሪክ ሽሚያ ይመስለኛል። ለአሁኑ የሚያስፈልገን ዋናው ነጥብ፣ አሁን የምንነጋገርበት አገራዊ ተሐድሶ እውን የሆነውና ወደፊትም የሚቀጥለው በዚህ በርካት በአብዛኛው ያልተደራጁ ተዋኛን በሚርመሰመስበት ምኅዳር በተደረገው እና ወደፊትም ሊደረግ በሚችለው ግፊት እና ሊያጋጥም በሚችለው ቀውስ መሆኑን ማስታወስ ነው። በዚህ ምኅዳር የሚፈጠር ቀውስ፣ “ልኩን” ካለፈ በመንግሥትና በፖለቲካ ልሒቃን ላይ ተጽዕኖ ከማሳረፍ አልፎ ወደ አገራዊ ብጥብጥ ሊከተን ይችላል። በተቃራኒውም፣ ምኅዳሩ ውስጥ የሚፈጠረው ሙቀትና ግፊት ከተቀዛቀዘና “ከልኩ” ከወረደ፣ ቀድሞ ወደነበርንበት አምባገነናዊ ሥርዐት መመለሳችን የጊዜ ጉዳይ ብቻ ይሆናል።

አሁን ባለው አሰላለፍ፣ ግፊት ሊፈጥር የሚችለው ሕዝባዊ ኀይል አልተደራጀም። በከፊል ተደራጅቷል በሚባልበት ቅርጹ ደግሞ በአብዛኛው የተደራጀው በብሔር መስመር ነው። በብሔር መስመር የመደራጀትን ጥቅምና ጉዳት ማውሳት ለዚህ ውይይት አንኳር ጉዳይ ባይሆንም፣ በየብሔሩ ብቻ የተደራጀ ጉልበት አገራዊ ትስስርና ቅርጽ የሚሰጠው ጠንካራ

አደረጃጀት እና አካል ካላገኘ የቀውስ ተዋናይ የመሆን እድሉ ከፍ ያለ መሆኑን ማስታውስ ግዴታ ነው። በተግባርም በቂ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች አይተናል።

የዚህ ምኅዳር ጣጣ ውስብስብ ነው። ወደ ቀውስ ሊያመራ የሚችልባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው። አምባገነናዊ ሥርዓትን ለመቃወም የሚጀመር ንቅናቄ "ልኩን" አልፎ ወደ ማኅበረሰባዊ ቀውስ ሊከተው ይችላል። በተቃራኒውም የለውጥ ወቅት የሚፈጥራቸው የሕግ እና ሥርዓት መላላትና የተጋነነ የነጻነት ስሜት ወደ ቀውስ ሊያንደረድሩት ይችላሉ። የተሐድሶ ወቅት አንዱ ፈተና ሽግግርን እና የቀውስ አዝማሚያን አቻችሎ ማለፍ ነው።

- ***ምኅዳር ሁለት፤ የኢሕአዴግና የመንግሥት ምኅዳር፤ ውስጣዊ ቀውሱና ተሐድሶ***

የፓርቲና የመንግሥት ተቋማት የተደበላለቁበት አገር ባይሆን ኖሮ ገዢውን ፓርቲ እና መንግሥትን በየራሳቸው ምኅዳር አስቀምጦ መተንተን ያስፈልግ ነበር። አሁን ሁለቱ በፍጹም ትዳርና ተሳክሮ ስለሚገኙ፣ እንደዚያው ማየቱ ያስፈልጋል።

በአገራዊው ምኅዳር የተፈጠረው ግፊትና ቀውስ በኢሕአዴግ እና በመንግሥት ውስጥ ትልቅ ቀውስ ፈጥሯል። ይህ ቀውስ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ኢሕአዴግን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ ወደ አዲስ ምእራፍ ገፍቶታል። አዲሱ የድርጅቱ ምእራፍ እንዴት እንደሚቋጭ ባናውቅም፣ የጅምሩ አንድ ገጽታ ለአገራዊ ተሐድሶ ቁልፍ ግብአት ሆኗል። በኢሕአዴግ ምኅዳር ውስጥ እየሆነ ያለውና የሚሆነው ቢያንስ ለቀጣዮቹ በርካታ ወራት ትልቅ አገራዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ጉዳይ ሆኖ ይቆያል።

መንግሥታዊ ተቋማት አሁን ባሉበት ሁኔታ ከኢሕአዴግ ተነጥለው ለአገራዊ መንቃቃቱም ሆነ ተሐድሶው ነጻ አስተዋጽኦ ማድረግ አይችሉም። በአጭሩ፥ ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ፣ መንግሥት በኢሕአዴግ ውስጥ የሚሆነው ለውጥ እስረኛ ነው። የመንግሥት ተቋማትን ገለልተኛነትና ተአማኒነት ከመሠረቱ የመቀየር ሥራ አስቸኳይና አስፈላጊ የሚሆነውም ለዚህ ነው። በዚህ በኩል የተጀመሩ ለውጦች አሉ። ጅምሮቹ ቢደነቁም ፍኖተ ካርታ በሌለበት የሚካሔድ በመሆኑ ቀጣይ የሒደቱን ይዘት አናውቀውም።

ይህ ማለት የመንግሥት አካላት እስከዚያው ምንም ሚና መጫወት አይችሉም ማለት አይደለም። አሁን የተፈጠረውን መንፈስና ሁኔታ ተጠቅሞ፣ ተቋማቱ ውስጥ ያሉ ተቀጣሪዎች የሕጎች መሻሻልን ሳይጠብቁ አነስተኛ ነገር ግን ጠቃሚ መሻሻሎችን በየግላቸው እንዲያደርጉ ግፊት ማሳደር ይቻላል። ከፋቱ፣ ይህ የተደራጀ ሲቪል ማኅበረሰብ እና የነቃ ሚዲያ ይፈልጋል። ይሁንና፣ ጅምሩን ማበረታታት ከተቻለ በሒደት የመንግሥት አካላት መሻሻሎችን ማድረጋቸው አይቀርም። ለምሳሌ፣ መገናኛ ብዙኀን የወህኒ ቤት አበሳዎችን በስፋት መዘገብ መጀመራቸው፥ ወህኒ ቤቶቹም ከቀድሞ በተሻለ በራቸውን ለተመልካች መክፈታቸው በሕጎችና በተቋማዊ መሻሻል የመጣ ሳይሆን፥ ከወቅቱ የለውጥ መነቃቃት የሚቀዳ ነው። ለውጡ ስር ካልሰደደ ወደኋላ እንደሚመለሱ ግልጽ ሆኖ ይታያል።

- ***ምኅዳር ሦስት፤ የአገራዊ መነቃቃት እና ተሐድሶ ምኅዳር***

የለውጥ ደጋፊ የሆኑ ኀይሎች በተስፋና በስጋት የሚዋከቡበት ምኅዳር ነው። በተቃራኒው፣ ምኅዳሩን በጥርጣሬ ወይም በጥቅሜ ተነካ ኩርፊያ የተሞሉ ተዋንያን በስሜት የሚወራጩበት ነው። አሁን በአገር ደረጃ ያለነው እዚህ ምእራፍ መጀመሪያ ላይ ይመስለኛል። ትልቅ አገራዊ መነቃቃት አለ፤ በርካታ የአገራዊ ተሐድሶ (ሪፎርም) ምልክቶች እየታዩ ነው፤ ተቋማዊ ግን አልሆኑም። አምባገነናዊ አስተሳሰብና ተቋማዊ ባህሎች ወደማፈግፈግ የሚገቡበት ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የሚዳከሙበት ምእራፍ አይደለም። ከፍተኛው የቅልበሳ አደጋም ያለው እዚህ ነው። ይህ ምእራፍ በስኬት "ሲጠናቀቅ" ከአምባገነን ሥርዓት የመውጣ ሒደቱ የበለጠ አስተማማኝ ይሆናል።

"አገራዊ መነቃቃት" በይፋ የምናየው ከአብዛኛው ሕዝብ እና ተዋን ያን የሚሰማው የለውጥ ተስፋና መነቃቃት ነው። "አገራዊ ተሐድሶ" የምለው በዋናነት የፖለቲካ ምኅዳሩ ለብዙ ተዋንያን ክፍት መደረግ (ፖለቲካል ሊበራላዜሽን) የሚጀመረበትን ወቅት ነው። ይህም ጥልቀቱ ቢለያይም የሕግ፣ የተቋማዊ አሠራሮችን ወዘት ለውጥ የሚያስከትል ነው። ባለንበት ሁኔታ፣ አገራዊ ተሐድሶው በብቸኝነት በኢሕአዴግ ባለቤትነትና ፈቃድ እየተካሔደ ነው። ለዚህም ነው ለውጡ አሁን ባለበት ደረጃ የኢሕአዴግ ውስጣዊ መስተጋብር እስረኛ ነው ያልኩት። ኢሕአዴግ ለውጡን ማስቆም አይችልም

የሚል የዋህ አመለካከት ቢኖረን እንኳን፣ ለውጡን ወደብጥብጥ ማሸጋገር እንደሚችል ማስታወስ አይሳነንም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። አገራዊ ተሐድሶው በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቀጥል አንዱ ማረጋገጫ

በዚህ ምኅዳር ውስጥ እስከአሁን ጎልተው የሚታዩት ኢሕአዴግ እና በሚገባ ያልተደራጀ የሕዝብ እንቅስቃሴ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስካሁን ለዚህ ምኅዳር የሚመጥን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ፍላጎትና አቅም እንዳላቸው እያሳዩ ነው። መንግሥት በተቋም ደረጃ የአገራዊ ተሐድሶው አካል ለመሆን ቢያንስ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የጀመረ ቢሆንም ተቋማዊ ጉዞው ብዙ ጥረትና ጊዜ የሚወስድ መሆኑ አያጠራርጥርም።

አሳሳቢው ነገር፣ ተቃዋሚዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ እና ባህላዊ/ማኅበራዊ ተቋማት እዚህ ምኅዳር ውስጥ ሲንቀሳቀሱ አለመታየቱ ነው። የመገናኛ ብዙኀን ዘርፉም ገና ከእስር መፈታቱ ነው። እነዚህ አካላት በፍጥነት ወደምኅዳሩ የሚገቡበትና ሚናቸውን የሚጫወቱበት ሁኔታ ካልተፈጠረ፣ አገራዊ ተሐድሶው ከእነርሱ ሊያገኝ ይገባና ይችል የነበረውን ትልቅ እገዛ ሳያገኝ ይቀራል፤ በውጤቱም ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል። የአገራዊ ተሐድሶው ባለቤትነት በጠ/ሚሩ እና በድርጅታቸው ብቸኛ ሚና ላይ ተንጠልጥሎ ብዙ መጓዝ የለበትም። አለዚያ አምባገነናዊ ዝንባሌዎች ተመልሰው ያገነግናሉ። በሌላ በኩል፣ አኩራፊ ኀይሎች ምን ሊያደረጉ እንደሆነ እየተመለከትን ነው።

ስለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ቡድኖች ሲነገር በተለምዶ ሁሉም ዴሞክራሲ ፈላጊዎችና ዲሞክራቶች ተደርገው ይቆጠራሉ፤ በስሕተት። በመሠረቱ፣ ሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን ክፉ ሥራ መቃወም ብቻውን የዴሞክራሲያዊነት ማረጋገጫ ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም። ስለዚህም፣ ተቃዋሚዎች የአገራዊ ተሐድሶና ሽግግር ሒደቱ ባለቤቶች ሆነው እንዲሳተፉ ስንጠይቅ፣ ገንቢ ብቻ ሳይሆን አፍራሽ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ባለመዘንጋትም ጭምር ነው።

### ምኅዳር አራት፤ አገራዊ የዴሞክራሲ ሽግግር

በመሠረቱ ይህ ምእራፍና ምኅዳር ቀድሞት ካለው (3) ጋራ አብሮ ሊታይ የሚችል ነበር፤ በተግባርም መደራረባቸው የሚቀር አይደለም። ይሁንና ሁለቱን ነጥሎ መመልከቱ በየደረጃው ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ተግባራት ለይተን እንድንመለከት ያስችሉናል። በዚህ ምኅዳር ንቁ ሚና የሚጫወቱ በርካታ ተዋንያን መኖራቸው ለሽግግሩ የሞትና የሽረት ጉዳይ ነው። ጠ/ሚ ዐቢይና ኢሕአዴግ (ውስጣዊ ክፍፍሉን ለጊዜው ባናሰላው እንኳን) ብቻቸውን፥ ከአገራዊ መነቃቃትና ተሐድሶ ያለፈ ነገር ሊሠሩ አይችሉም።

በቀዳሚዎቹ ምኅዳሮች የሚካሔዱትን ለውጦች ያለግልጽ ፍኖተ ካርታ መጀማመር ይቻል ይሆናል። አገራዊ የዴሞክራሲ ሽግግር (ዲሞክራታይዜሽ) ብዙዎች የተስማሙበትን ፍኖተ ካርታ የግድ ይላል። ይህ ስራ መጀመር ያለበት ቢዘገይ በሦስተኛው ምኅዳር ውስጥ ነው። በብዙ መልኩ፣ አገራዊ የዴሞክራሲ ሽግግር ቢያንስ የቁልፍ የተዋንያንን ሙሉ ተሳትፎ ግድ ይላል።

### ምኅዳር አምስት፤ የዴሞክራሲ ግንባታ ሙከራ

ይህ ምኅዳር፣ ለውጦች ተቋማዊ ቅርጽ ይዘው አገራዊ ሙከራችንን የምር የምንጀምርበትና የምናጎለብትበት ነው። ዝርዝሩ ለጊዜው አያስፈልገንም ብንል እንኳን፣ ሌሎቹን ምኅዳሮችና ደረጃዎች በተአምር ዘሎ እዚህ መድረስ እንደማይቻል ማወቅ ወገብን አጥብቆ ለመጠበቅ ይረዳል። ዝርዝሩን ስንደርስበት ለማውሳት እናሳድረው።

ሲጠቃለል፣ እየሆነ ያለውን በየፈርጁና በየምኅዳሩ ለያይቶ መመልከት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ከጠቀምኩ የሚበቃ ይመስለኛል። እንደ ውይይቱ ጉዳይ፣ ምኅዳሮቹን ቀያይሮ መመልከትም ይሚቻል ነው። ቀሪው እያንዳንዱ ያገባኛል ባይ፣ የየራሱን ምኅዳር መተንተን፣ ከሌሎቹ ምኅዳሮች ጋራ ያለውን መስተጋብር በሒደት ማጤን ነው። ለዚህ ጽሑፍ መዳረሻ ስለማይጠቅም ወደ ዝርዝሩ አንገባም።

ማጠንጠኛው፣ ገዢው ግንባር አንድ የለውጥ ተዋናይ እና ምኅዳር መሆኑን ደጋግሞ መጥቀስ የሚያስፈልገው ማንኛውም አገራዊ የተሐድሶ እና የሽግግር (ሪፎርም እና ትራንዚሽን) ሒደት ከአንድ በላይ ተዋንያን እና ምኅዳሮች እንዳሉት ማጠየቅ ነው። ለምሳሌ፣ ሌላው የለውጥ ተዋናይ መሆን የሚችለው አካል የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጎራ ነው። በዚህ ጎራ ምኅዳር ውስጥ የሚከናወነው ነገር በኢሕአዴግ ምኅዳር ውስጥ ከሚደረገው የተለየ ነው፣ ነገር ግን ብቻውን ተገንጥሎ የሚቆም አይደለም። በመጨረሻ ሁለቱም ተዋንያን ከየምኅዳራቸው መስተጋብር የቀዱትን ይዘው ከፍ ወዳለው አገራዊ ምኅዳር ይፈሳሉ። የአገራዊ ምኅዳሩን ይዘት የሚወስኑት ሁለቱ ብቻ አይሆኑም። እነዚህ አካላት እና ምኅዳሮቻቸው የተለያዩ ቢሆንም የተገለሉ ደሴቶች ግን አይደሉም። የአንዱ ውስጣዊ ምኅዳር መስተጋብርና ውጤት የሌላውን ተዋናይ ውሎ እና የምኅዳሩነ ሕይወት ሳይነካው አያልፍም።

የፓርቲዎች ውስጣዊ ተሐድሶ እና ሽግግር ውጤት በየራሳቸው ርዕዮተ ዓለማዊ፣ የፖሊሲ፣ የስልት እና የአደረጃጀት ይዘት የሚለካ ነው።[13] በአገራዊው ምኅዳር የምናየው ተሐድሶ እና ሽግግር የሚመዘነው ግን በተሐድሶ ወቅት በሚወሰዱ አስቸኳይ እርምጃዎች[14]፣ የሕግ የበላይነትን በሚያሰፍኑ አዳዲስ አሠራሮች፣ እና በገለልተኛ አገራዊ ተቋማት ግንባታ ጅማሮ ነው። አስቸኳይ እርምጃዎቹ ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆኑም ተሐድሶውን ለሽግግር ለማድረስ የሚበቁ አይደሉም። ለዚህም ነው የተሐድሶ ወቅት ስሜት እና አስቸኳይ እርምጃዎች ብቻቸውን እንዳያዘናጉን የሚያስፈልገው።

ይህን ሁሉ ያመጣሁት በኢሕአዴግ ምኅዳር ውስጥ እየተካሔደ ያለውን መስተጋብርና ገና ቁርጡ ያልለየለት የተሐድሶ ሒደት፣ በአገራዊው ምኅዳር ላይ እየሆነ ካለው ወይም እንዲሆን ከምንመኘው ለይተን እንድንመለከተው ነው። ሁለቱ ምኅዳሮች በብዙ ገጸቸው ተነባብረው ይታያሉ፤ መስተጋብራቸውም በጣም ጥልቅ ነው። ሆኖም አንድ አይደሉም። በኢሕአዴግ ውስጣዊ ምኅዳር ውስጥ የሚደረገውን ትግልና ተሐድሶ በባለቤትነት መምራት ያለባቸው የድርጅቱ አባላት ናቸው። ሆኖም የፓርቲው አባላት ያልሆኑ፣ ነገር ግን የኢሕአዴግ ተሐድሶ በአገራዊው ምኅዳርና የሽግግር ሒደት ላይ ያለውን ቁልፍ ሚና የሚረዱ ዜጎች በኢሕአዴግ ውስጥ የሚንተከተከውን ለውጥ በግዴለሽነት ሊያዩት አይችሉም። ምንልባትም በኢሕአዴግ ውስጥ የሚታየውና ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድና ቡድናቸው የሚመሩት የለውጥ እንቅስቃሴ እንዳይከስም ድጋፍ የመስጠት ስልታዊ ግዴታ ይኖርባቸዋል፤ ለረጅም ጊዜ ጥቅማቸው ሲሉ። በኢሕአዴግ ምኅዳር ውስጥ ያለው የለውጥ ግለት ቢቻል የበለጠ እንዲጠናከር፣ ካልሆነም ቢያንስ አገራዊ ተሐድሶው ወደሽግግር ተለውጦ ከማይቀለበስበት ደረጃ እስኪደርስ ባለበት እንዲቆይ መመኘት፣ አልፎም ቢያንስ ስልታዊ እገዛ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው።

የኢሕአዴግ ተሐድሶ ድርጅቱን ወደየት እንደሚያሸጋግረው አናውቅም። የድርጅቱ ተሐድሶ ቅልበሳ አገራዊ ተሐድሶውን ሊያከስም የሚችልበት እድል እንዳለ ቀደም ሲል ገልጫለሁ። እዚህ ላይ ኢሕአዴግን እንደዋና ተዋናይ ባነሣም፣ ቀደም ሲል በተሳለው ሒደት በሁሉም ደረጃ የተደራጀ ሕዝብ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰቡ፣ እና ሌሎች ቡድኖች ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ግልጽ ነው። እነዚህ ተዋንያን በየራሳቸው ምኅዳር ምን እየተካሔድ እንደሆነ ማጤን፣ የየምኅዳራቸውን መስተጋብርና ቁመና ማጠናከር፣ አገራዊ ሽግግሩ እውን እንዲሆን ግፊትና አስተዋጽኦ ለማድረግ መዘጋጀት አለባቸው።[15] ጠ/ሚ ዐቢይ ፍኖተ ካርታቸውን እንዲያቀርቡ የሚጠየቅበት አንዱ መነሻም፣ እነዚህ ከኢሕአዴግና ከመንግሥት ውጭ ያሉ አካላት እንዴት፣ መቼና በምን ጉዳይ የሒደቱ ይፋዊ አካሎች እንደሚሆኑ መታወቅ አለበት ከሚል እምነት ነው።

## 3፤ የአገራዊ ተሐድሶ እና ሽግግር ቁልፍ ይዘቶች

በአገራዊ ተሐድሶ ወቅት በዋናነት ትእምርታዊ ዋጋቸው ከፍ ያለ፣ የፖለቲካውን ድባብ ወደበጎ አቅጣጫ ሊቀይሩ የሚችሉ፣ እንዲሁም አስቸኳይ የእርምትና የማነቃቂያ እርምጃዎች የሚወሰዱበት ምእራፍ ነው። በዚህ በኩል ጠ/ሚ

---

[13] ኢሕአዴግ ውስጥ የርዕዮተ ዓለም ሽግሽግ ወይም ለውጥ ስለመኖሩ ውይይቶች መጀመራቸው ይታወቃል። እንድርያስ እሸቴ (ፕ/ር) ያቀረቡት መወያያ አንድ አብነት ነው። በተቃዋሚዎች ጎራ ከርዕዮተ ዓለም ይልቅ የስልት ሽግሽግ ወይም ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ይቻላል።

[14] አስቸኳይ እርምጃዎች ከሚባሉት ለምሳሌ የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት፣ በመጠፎ ስማቸው የሚታወቁ ባለሥልጣናትን ገለል ማድርገ የሚጠቀሱ ናቸው። ይህን መሰል በርካታ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው።

[15] እነዚህ ተዋንያን በተናጠላዊ ምኅዳራቸው ምን እያደረጉ እንደሆነ መመርመር አስፈላጊ ነው።

ዐቢይ ተስፋ ሰጪ ሥራ ጀምረዋል የሚል እምነት አለኝ። እንዲያውም፣ በጣም ፈጣንና እርምጃዎችን ጭምር እያስተዋወቁ ነው ማለት ይቻላል። የፖለቲካ እስረኞች መፈታት መጀመር፣ እጅግ ጋባዥ እና አገራዊ ስሜትን የሚያነቃቁ ንግግሮችና ጉብኝቶች፣ በመንግሥት ስም ያቀረቡት የይቅርታ ጥያቄና ጥፋትን ሳያድበሰብሱ የማመን ፖለቲካዊ ድፍረት፣ ከውጭ አገሮች እስረኞችን ማስፈታት፣ ለመከላከያው አዛዦች ከፖለቲካ ወገንተኝነት እንዲወጡ የሰጡት ማብራሪያና መመሪያ፣ በመጥፎ ዝና የሚታወቁትንና የሚፈሩትን በተለይ የኤታማዦር ሹሙንና የጸጥታውን ዘርፍ ሐላፊ ከስልጣናቸው ማንሳታቸው ወዘተ በጭራሽ ሊናናቁ የማይችሉ የለውጥ ምልክቶች ናቸው። በተለይም እነዚህን እርምጃዎች ከአራት ወራት በፊት አገሪቱ ከነበረችበት ሁኔታ ጋራ አነጻጽረው ሲመለከቷቸው የበለጠ ክብደት የሚሰጣቸው ይሆናሉ።

በዚህ ሚዛን ካየነው አገራዊ ተሐድሶው ሊሳካ ይችላል። ሆኖም ይህን ለማስረገጥ ተጨማሪ ማሳያዎችና ማስተማመኛዎች ያስፈልጋሉ።  የተሐድሶ ዘመን ቁልፍ መመዘኛዎች ሙሉ ዝርዝር እንደ አገሩና እንደ ሒደቱ የሚለያዩ ናቸው። አገራዊ ተሐድሶ በተለያዩ ፓርቲዎችና ቡድኖች ድርድር የሚቀየስ ሲሆን ደግሞ ዝርዝሩ የተደራዳሪዎቹ ፍላጎትና ቁመና ነጸብራቅ ይሆናል። በእኛ ሁኔታ፣ አገራዊ ተሐድሶው የተጀመረው በከፊል ብቻ በተደራጀ ሕዝባዊ ግፊት፣ በፖለቲካ ቀውስ እና ኢሕ አዴግ ውስጥ በተፈጠረ አዲስ መስተጋብር ነው። የተቃዋሚ ቡድኖች ድርሻ በአብዛኛው በሕዝባዊ አመጹ ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ እንጂ ራሱን ችሎ የወጣ አይደለም። ይህም፣ የአገራዊ ተሐድሶውን አጀማመር ብቻ ሳይሆን የቀጣይ ሒደቱን ቅርጽና ይዘትም በእጅጉ ሊወስን የሚችል መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ይህን ከግምት በማስገባት፣ በአገራዊ ተሐድሶው ወቅት ሊጀመሩ ወይም ሊከናወኑ የሚገባቸውን፣ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራትን መለየት አስፈላጊ ይሆናል። በእኔ እምነት የአገራዊ ተሐድሶ ወቅት ቁልፍ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

1፤ የፖለቲካና የጸጥታ ቀውሶችን የሚያስቀሩ ወይም እንዳይባባሱ የሚያደርጉ እርምጃዎችን መውሰድ

2፤ የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት፣ በቀላሉ ሊስተካከሉ የሚችሉ አፋኝ አሠራሮችን በፍጥነት ማስተካከል

3፤ አፈናን የሚያቋቁሙ አሠራሮችን፣ ሕጎችንና የፍትሕ ተቋማትን ለመለወጥ የሚያስችል ሥራ መጀመር

4፤ የመንግሥት ተቋማት ቢያንስ መሠረታዊ አግልግሎቶችን በተጠናከረ መልኩ መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ማስቻል

5፤ የጸጥታና የመከላከያ ተቋማትን ፖለቲካዊ ወገንተኝነት ለማስቀረት/ለመቀነስ የሚያስችሉ እቅዶችን አውጥቶ ቁልፍ ለውጦችን ለማስተወቅ ሥራ መጀመር

6፤ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋራ ድርድር ለመጀመር የሚያስችሉ መሠረታዊ ሁኔታዎችን መፍጠር

7፤ ገዢው ፓርቲ በቢሮክራሲ ውስጥ ያለውን ፍጹም ጣልቃ ገብነት የሚያስቆም ሥራ መጀመር

8፤ ትልልቅ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የማጣራት ሥራ መጀመር

9፤ አገራዊ ጉዳታቸው ከፍ ያሉ የዘረፋ እና የሥልጣን መባለጎችን የማጣራት ሥራ መጀመር

10፤ የአገራዊ ሽግግሩ ሒደትና ይዘት የሚያሳይ ንድፍ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት፣ በዚህም ላይ በተለይ ከተቃዋሚ ድርጅቶችና በሲቪል ማኅበራት ጋራ መወያየት[16]

አሁን ያለነው በአገራዊ ተሐድሶ ጅማሮ ላይ ነን ብያለሁ። ከዚህ አንጻር ቀደም ሲል ከለየኋቸው ቁልፍ ተግባራት አብዛኞቹ እየተፈጸሙ ወይም እየተጀመሩ መሆኑ የመነቃቃቱ ምክንያቶች ናቸው። ጠ/ሚ ዐቢይ የጀመሯቸውን የለውጥ እንቅስቃሴዎች በመደገፍ የሚታየው ሰልፍና ሌላም አይነት ማበረታቻ ለዚህ ጥሩ ማረጋገጫ ነው። ሆኖም፣ ከተራ ቁጥር

[16] ይህ ንድፍ ፍኖተ ካርታ፣ የጋራ መግባባት ተደርጎበት ቢጸድቅ ለአገር እጅግ ይጠቅማል። ሆኖም በሁሉም የፍኖተ ካርታው ጉዳዮች ላይ መስማማት ጊዜ የሚወስድ ከሆነ፣ ቁልፍ በሚባሉት ላይ መወያየት፣ ልዩነቶችን አንጥሮ ማውጣት፣ ከነልዩነቶቹ በአስማሚ ጉዳዮች ላይ በጋራ ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል መውጫ መፈለግ ይገባል። ለምሳሌ፣ ሕገ መንግሥት ካልሻሻለ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ሊኖር አይችልም ከሚሉ ኀይሎች ጋር መግባባት የሚቻለው በዚህ መሰሉ ፎኖተ ካርታ ነው።

አንድ እስከ አምስት ያሉት መጀመራቸውንና እንደሚቀጥሉ ብንተማመን እንኳን፣ ቀሪዎቹ (6-10) መጀመራቸውን አስረግጦ መናገር አይቻልም። ነገሩን ለማሳጠር፣ በእነዚሁ በሦስቱ ላይ ብቻ አጭር አስተያየት ልስጥ።

በስደት ካሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋራ የተጀመሩ ንግግሮች አሉ፣ የተወሰኑትም ወደ አገር ቤት እየተመለሱ ነው። ኦነግ፣ ኦብነግ እና ግንቦት 7 የሽብርተኝነት ፍረጃቸው ከመነሣቱም በላይ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ንግግሮች መጀመራቸውም ይታወቃል። ይሁንና፣ እስከዛሬዋ ዕለት ደረስ፣ እነርሱ ወደ አገር ቤት ተመለሱም አልተመለሱም፣ መንግሥት ከተቃዋሚዎች ጋራ መቼ፣ በምን ማዕቀፍ፣ በምን ጉዳይ እንደሚነጋገር ወይም እንደሚደራደር የምናውቀው ነገር የለም። ኢሕአዴግ ቀደም ባሉት ዓመታት የሚተውነው የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርድር ድራማ እንደማይደገም ተስፋ ከማድረግ ባለፈ፣ የጠ/ሚ ዐቢይ አካሔድ ምን እንደሚመስል የምንረዳበት ፍኖተ ካርታም ሆነ ተጨባጭ ፍንጭ የለም።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ውጭ ያሉ ወገኖች (ሲቪል ማኅበረቡ፣ ማኅበረ ባህላዊ ተቋማት[17]፣ የሃይማኖት መሪዎች ወዘተ) በአገራዊ ተሐድሶው ሒደቱ ውስጥ የሚሳተፉበት ሁኔታ እስከ አሁን ግልጽ አይደለም። ጠ/ሚሩ በየንግግሮቻቸው ሕዝቡ የተጀመረውን ተሐድሶ እንዲደግፍና እንዲጠብቅ ተገቢ ጥሪ ያቀርባሉ። ይህ በተቋማዊ መንገድ ሊሳካ ስለሚችልበት መንገድ መንግሥታቸው ምን ዝርዝር እቅድ እንዳለው ግን አልነገሩንም። እርሳቸው በአገር ውስጥ ያደረጓቸው ሕዝባዊ ውይይቶች ለወቅቱ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ናቸው። ዘላቂና ተቋማዊ ቅርጽ ግን የላቸውም፤ ከክልል ጀምሮ በየደረጃው ያሉ መሪዎች ፈለጋቸውን እንደሚከተሉ የሰጡን ማረጋገጫም ገና አልደረሰንም። ክልሎች በፌደራል መንግሥቱ መሪ የሚንጸባረቀውን መንፈስ በተግባር ይከተሉታልን? የተወሰኑ የፖለቲካ እስረኞችን ከመልቀቅ ባለፈ፣ ክልሎች ምን እያደረጉ ነው፣ ምንስ አስበዋል? ገና ጥያቄ ላይ ነን።

ለምሳሌ፣ የሕግ እና ፍትሕ አማካሪ ምክር ቤት/ጉባዔ በዘርፉ ያለውን ስር የሰደድ ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ሐሳቦችን እንዲያቀርብ ታስቧል። ጉባዔው 13 አባልት ተሰይመውለታል፤ በጠቅላይ አቃቤ ሕጉ እየተመራ ተጠሪነቱ ለጠ/ሚሩ ይሆናል ተብሏል። አባላቱ በምን አስተዋጽዖዋቸውና ልምዳቸው እንደተመረጡ ለሕዝብ አስቀድሞ አለመገለጹ ስሕተት ቢሆንም፣ በአባላቱ ላይ ጠንካራ ተቃውሞ ሲቀርብ አልሰማሁም። የጉባዔው መቋቋም አስፈላጊ ነው። ይሁንና ጉባዔው ሲቋቋም ሕዝቡ፣ ቢያንስ ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሲቪል ማኅበራት፣ እጩዎችን የመጠቆም እድል እንዲያገኙ ቢደረግ አግባብ ነበር እላለሁ። የጉባዔው የሥራ ዘመን ሦስት ዓመታት እንደሚሆን ተገልጿል። የጉባዔው ዝርዝር ሥራና ሃላፊነት ባልተገለጸበት፣ ስለሥራ ዘመኑ ብዙ ማለት አይቻልም። የፍትሕ ሥርዓቱ ማሻሻያ ካለው ቁልፍ ሚና አንጻር፣ የጉባኤው ጉዳይ አሁንም ቢሆን ቢያንስ ከተቃዋሚዎች፣ ከባለሞያዎች ማኅበራት እና ከፍትሕ ሥርዓቱ ሰለባዎች ጋራ የምር ውይይት ካልተደረገበት፣ የጉባዔው ሥራ ፍሬያማ ቢሆን እንኳን ፖለቲካዊ ተቀባይነቱ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ማሳሰብ አስፈላጊ ይሆናል። ይህም መልሶ የሚወስደን፣ የጉባዔውን መቋቋምና የሥራውን ትርጉም የምንመዝንበት ፍኖተ ካርታ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፖለቲካዊ ተሐድሶውን በይቅርታ መንፈስ እንዲመራ ጠንካራ ፍላጎት እንዳላቸው ግልጽ ነው። ሆኖም ይቅርታው በደፈናው በማለፍ ሊሆን እንደማይችል የታወቀ የተረዳ ነገር ነው። የሽግግር ፍትህ (ትራንዚሽናል ጀስቲስ) የሒደቱ ቁልፍ መሆን እንዳለበት የሚከራከሩ አሉ። እርግጥ ጠ/ሚሩ ከተጋረጡባቸው ትልልቅ ፈታኝ ሁኔታዎ አንጻር የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ባይሆን ብዙ የሚያስገርም አይሆንም። በሐላፊነት መጠየቅ ይቆይ ቢባል እንኳን፣ የተፈጸሙትን ትልልቅ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ወንጀሎች የሚመረመሩበት ሥርዐት እንዲበጅ ዝግጅት ማድረግ ግን ያስፈልጋል።[18]

ዴሞክራሲያዊ ሽግግር የተሟላ የሚሆነው ቢያንስ ከፍተኛ ወንጀሎች ተመርምረው ጥፋተኞች ሲቀጡ አለዚያም ይቅርታ ሲጥይቁ ነው። እርግጥ፣ ገና ከጅምሩ በዚህ ላይ ማተኮር በተሐድሶ እና በሽግግር ጅማሮው ላይ እንቅፋት ሊፈጠር እንደሚችል የታወቀ ነው። በሐላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉ ሰዎች፣ የለውጥ ሒደቱን በማስቆም ወይም አቅጣጫ በማስቀየር ከተጠያቂነት የሚያመልጡበትን መንገድ ማፈላለጋቸው አይቀሬ ነው። ይህን ምልክት አላየንም ብለን አንዋሽም። ይሁንና፣ ከሌሎች አጣዳፊና አስፈላጊ ጉዳዮች አንጻር ትኩረትን በለውጡ ሒድት ላይ ማድረግ እንደሚሻል፣ እንዲያውም

---

17 ምናልባት በብቸኝነት ሊጠቀስ የሚችል ምሳሌ ቢኖር የአባገዳ መሪዎች ድምጽ ተደጋግሞ መሰማት መጀመሩ ብቻ ነው። ሌሎች ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ማኅበረ ባህላዊ ተቋማት ግጭት ለማብረድ ካልሆነ በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ድምጻቸው አይሰማም። ወደፊት ማኅበረ ባህላዊ ተቋማት በፖለቲካ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና መወያየት ያስፈልግ ይሆናል።

18 ሁለት አማራጮች አሉ። አንዱ ራሱን የቻለ ጉባዔ/ተቋም ማቋቋም ነው። ሁለተኛው አማራጭ የሰብአዊ መብት ኮሚሽኑን አመራር በመቀየርና አሠራሩን በማስተካከል ምርመራውን እንዲያደርግ በጊዜ ገደብ የተወሰነ አዲስ ሃላፊነት መስጠት ነው። ይህ ተቋም አሁን ባለበት ሁኔታ አንዳችም ተአማኒነት የሌለው፣ የኢሕአዴግ ድርጅታዊ ተቀጽላ ሆኖ የኖረ እርባና ቢስ ተቋም ነው። አመራሩን መቀየር የግዴታ ነው።

ሊጠየቁ ለሚችሉት ሰዎች መተማመኛ በመስጠት ጭምር የለውጡ እንቅፋት እንዳይሆኑ መሞከርን የሚመክሩ አይጠፉም። በተቃራኒው ወንጀለኞችን ተጠያቂ የማድረጉ ሥራ አሁን በተደረሰበት ደረጃ ጭምር መከናወን አለበት የሚሉ ድምጾች ይሰማሉ። ፍትሕ የተጠያቂነት ባህልን ከመፍጠርም ይሁን የተጎጂዎችን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል። ፍትሕ የሽግግሩ ግብአትም ውጤትም ሊሆን ይችላል። ሆኖም ፍትሕ ሊሰጥ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር መቅደም አለበት። ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ የሰብአዊ መብት ጥሰት እና የስርቆት ወንጀሎችን የመመርመር ሥራ በተቻለ ፍጥነት እንዲጀመር ከማድረግ ያለፈ መጠየቅ የሚቻል አይመስለኝም።

ወደ ሌላ ነጥብ እንሂድ። የገባንበት ቀውስ አንዱ ምንጭ ቢሮክራሲው የፖለቲካ ድርጅት ተቀጥላ መደረጉ ነበር። ይህ ባህል በይፋ ተወግዞ በሕግ በሒደት ወደተቋማዊና ሞያዊ አሠራር መለውጥ አለበት። በሦስት ወር ውስጥ ይህንን ለውጥ መጠበቅ የዋህነት ይሆናል። የረጅም ጊዜው ለውጥ አካል መሆኑን ለማረጋገጥ ይህንኑ የሚያመላክት ፍኖተ ካርታ ያስፈልገናል።

እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያስፈልገው ሁሉንም የአገሪቱን ችግሮች በዚህ የተሐድሶ እና የሽግግር ዘመን ሥራዎች ውስጥ ማካተት እንደማይቻል ነው። ለምሳሌ፣ የትምህርት ጉዳይ በተሐድሶ እና በሽግግር ዘመን የሚሠራ አይደለም፤ እርጋታና በሕዝብ መመረጥን የሚጠይቅ ተግባር ስለሆነ።

እዚህ የዘረዘርኳቸው ቁልፍ የተሐድሶና የሽግግር ዘመን የማለዳ ሥራዎች በተለያየ መልኩ እንደተጀመሩ እናውቃለን። ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ሌላ አካል ስለጅምሮቹ እዚህም እዚያም የፈነጠቁት መረጃ አለ። ሆኖም በቂና አስተማማኝ መረጃ የለንም፤ የምንከታተልበት መንገድም የለም። እስካሁን የተከናወኑትን ለውጦች፣ በኢሕአዴግም ይሁን በአገሪቱ ውስጥ ከቀጠለው አለመረጋጋት አንጻር ከመዘንነው፣ ፍኖተ ካርታው ባለፉት መቶ ቀናት ተዘጋጅቶ መቅረብ ነበረበት ብሎ መውቀስ ምናልባት ርትእ የጎደለው ወቀሳ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም አስቸኳይነቱን ግን አይቀንሰውም። አገር የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቃል ብቻ እንደማስተማመኛ እና እንደማነቃቂያ ተቀብሎ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልም። ቢያንስ ቢያንስ ዝርዝሩ ቀርቦ፣ ወዴት፣ እንዴትና መቼ እንደምንደርስ ማወቅ ግዴታ ነው። ለለውጥ ሒደቱ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ድጋፍ፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ትችት መስጠት የሚቻለው ቢያንስ ቢያንስ ይህን መሰሉ ጊዜያዊ ፎኖተ ካርታ ሲኖረን ብቻ ነው። እንደአስፈላጊነቱም በምክክርና በክርክር ሊሻሻል ይችላል። ፍኖተ ካርታው በአገሪቱ መሪና በመንግሥታቸው ተዘጋጅቶ መቅረቡ ሌሎች አካሎችም ራሳቸውን እንዲፈትሹ፣ እንዲዘጋጁ የበለጠ እድል ይሰጣቸዋል።

**አንደኛ፤** እነዚህና ሌሎችም በመንግሥት የተመረጡ ተግባራት በዝርዝር ተቀምረው፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ መለኪያቸው ምን እንደሆነ ታውቆ፣ በዝርዝር መቅረብ አለባቸው። ምናልባት ከአገር ጥቅም አንጻር በምሥጢር መያዝ ያለባቸው ነገሮች ካሉም ይኸው ታውቆና ተገልጾ መደበቅ ይኖርበታል።

**ሁለተኛ፤** የትኛው አካል (ካስፈለገ በግለሰብ ደረጃ ሳይቀር ተገልጾ) የትኛውን ተግባር እንደሚያከናውነው ይፋ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ በተለይ መተማመንን ያዳብራል። እንደቀድሞው የአገር ጉዳይ የኢሕአዴግ የግል ጉዳይ ተደርጎ አለመወሰዱን ለማረጋገጥም ያስችላል። አሁን እንደማደርገው በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ካልሆነ፣ ያቺ ነጥብ በትክክል የት እንደምትገኝ ማወቅ አይቻልም።

**ሦስተኛ፤** እያንዳንዱ ተግባር በተናጠል እና አጠቃላይ የአገራዊ ተሐድሶውና ሽግግሩ ቁልፍ ተግባራት ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጁ በግልጽ መታቀድ እና የመከታተያ ዘዴ ማበጀትም ያስፈልጋል። (ለምሳሌ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሚመለከታቸው አስፈጻሚዎች በየወሩ ለፓርላማውና ለሕዝቡ ሪፖርት ሊያቅርቡ ይችሉ ይሆናል።)

**አራተኛ፤** ለዚህ ተግባር የሚውለው በጀት መታወቅ አለበት።

**አምስተኛ**፤ ልሳተፍ ባዩ እልፍ ቢሆንም፣ በዚህ እቅድ ነደፋና ዝግጅት ውስጥ በተቻለ መጠን በዛ ያሉ ባለሞያዎችንና ታዋቂ ግለሰቦችን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን፣ የሙያና የሲቪል ማኅበራት አባላት የሚያሳትፍ የቡድንና የጋራ መድረኮችን መፈጠር ያስፈልጋል።[19]

---

[19] ይኼ የሽግግር መንግሥት ከሚለው ሐሳብ የተለየ ነው።

## 4፤ አንኳር የለውጡን ባህርያት ፍለጋ

አሁን እየተደረገ ያለውን ተሐድሶ ይዘት እና የሽግግር ተስፋዎች በልካቸው ለመመዘን በየትኛው ምኅዳር ላይ እየተከናወኑ መሆናቸውን መለየት አስፈላጊ እንደሆነ ቀደም ሲል አንስቻለሁ። በአገራዊ ተሐድሶ ምኅዳር እየታየ ያለውን ወይም ሊሆን ይገባዋል የሚባለውን የለውጡን ይዘት በተመለከተ የሚከተሉት ሐሳቦች ተደጋግመው ይሰማሉ።

### ሀ፤ ጥገናዊ ለውጥ

ጠ/ሚ ዐቢይ በተከታታይ ነገር ግን በተበታተን መንገድ የሚነግሩንን እና ዘላቂ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ እርምጃዎቻቸውን እንደማረጋገጫ ከወሰድን፣ እንዲሁም ጅምሮቹ ካልተቀለበሱ፣ አገራዊ ተሐድሶው ወደ ሽግግር ሊገባ ይችላል። ይህ ሒደት በፍጥነቱም ሆነ በይዘቱ የነበረውን ከስሩ በመመንገል ሳይሆን ቁልፍ ሊባሉ የሚችሉ ለውጦችን በማስተዋወቅ ተሐድሶውን ለማስቀጠል ያለመ ይመስላል። እርግጥ ከተነሣንበት አንጻር ሲታይ፣ አሁን እየተካሄደ ያለው ለውጥ በጣም ፈጣን ነው። የተለመደውን አገላለጽ መጠቀም ግዴታ ከሆነ ይህን ሒደት “ጥገናዊ ለውጥ” ልንለው እንችላለን።

ጥገናዊ ለውጥን በደፈናው መጥፎ የሽግግር ስልት አድርጎ የማቅረብ አዝማሚያ ተደጋግሞ ያጋጥመኛል። ይህ አቀራረብ፣ ተገቢ የጥርጣሬ መነሻዎች ቢኖሩትም፣ “ጥገናዊ ለውጦችን” ሁሉ አንድ አይነት አድርጎ የማቅረብ መሠረታዊ ችግር አለበት። ጥገናዊ ለውጥን ጥሩም ሆነ መጥፎ፣ አስፈላጊ ወይም አላስፈላጊ፣ የሚቻል ወይም የሚመረጥ የሚያደርገው ለውጡ የሚካኼድበት ከባቢ ነው። በግቡና በአካሔዱ የሥርዓት ሽግግር ለማድረግ ያለመ ሒደት እስከሆነ ድረስ፣ የሚታገሡት አማራጭ የሚሆንበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ማስታወስ ያስፈልጋል። ከጥገናዊ ለውጥ በተቃራኒው ያለው አማራጭ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ ካለ፣ ጥገናዊ ለውጥ ማድረግ አርቆ አሳቢነት እንጂ አድሃሪነት አይሆንም። ቁም ነገሩ፣ ሁኔታው በሚጠይቀውና በሚፈቅደው መጠን፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያው የሽግግር ሥርዓት መካሔዱ ላይ ነው። ሆኖም በይዘቱም ይሁን በግቡ፣ የፖለቲካ ሥርዓቱን ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲ በማሸጋገር ፋንታ ሥልጣን ላይ ያለውን ኃይል በቦታው ለማቆየት ብቻ የተሰላ ከሆነ በወራት ዕድሜው ውስጥ የሚከስም ጅምር ይሆናል።

### ለ፤ ስር ነቀል ለውጥ

“ስር ነቀል” ለውጥ የአገራዊ ተሐድሶውም ይሁን የሽግግሩ ሒደት ዋና መገለጫ መሆን አለበት የሚለው አቅጣጫ ተደጋግሞ ይሰማል። አልፎ አልፎ “ስር ነቀል” የሚባለው ለውጥ አሁን ባለው አገራዊ የተሐድሶ ደረጃ ጭምር ሊተገበር ይገባል የሚል አስተያየትም ይደመጣል። “ስር ነቀል” ለውጥን ገና ከጠዋቱ መጠየቅ በመሠረቱ የአብዮታዊ ወቅት ባህርይ ነው። አሁን ያለነው ደግሞ በመደበኛው አስተምህሮ "አብዮት" ሊባል የሚችል አይደለም። ቢያንስ የኢሕአዴግ ውስጥ ተሐድሶ፣ ግፋ ቢል የአገራዊ ተሐድሶ ጅማሮ ላይ ብቻ ነን። "ስር ነቀል" ለውጥ የሚሉት ሰዎች ለለውጥ ያላቸውን ጉጉት በጠንካራ ቃላት ከመግለጽ አልፈው የሚነቀለው “ስር” የትኛው እንደሆነ፣ ምን ላይ ቆመው የትኛውን ስር ነቅለው መገላገለ እንደሚፈልጉ፣ መነቀል አለበት የሚሉትን ስር ሲነቅሉ ሌሎች ስሮችን እንደማይበጣጥሱ፣ በሚነቅሉት ስር ምትክ ካስፈለገ ወዲያውኑ የሚተኩት ያዘጋጁት "ስር" ስለመኖሩ የሚሰጡን በቂ ማብራሪያ የለም። እርግጥ ለዚህ አመለካከት መግነን አንዱ ምንጭ ለመነጋገር የሚበቁ የለውጥ ፍኖተ ካርታዎች አለመቅረባቸው የሚፈጠረው ጥርጣሬ ነው።

"ስር ነቀል ለውጥ [አሁኑኑ]" የሚሉት ወገኖቻችን የፖለቲካ ቀውሳችንን በመተንተን ደረጃ ብዙ የተለየ ነገር ሲያቀርቡ አልሰማሁም። አምልጦኝ ከሆነ ለመመልከት ፈቃደኛ ነኝ። የፖለቲካ ምኅዳር መዘጋት፣ የሕግ የበላይነት አለመኖር፣ መከላከያው፣ ፖሊስና ደኅንነቱ፣ የፍትሕ ሥርዓቱ፣ የአስፈጻሚው አካል ማን አለብኝነት፣ ከሕገ መንግሥት ጋራ የተያያዙ ጥያቄዎች እና የመሳሰሉትን ችግሮች በተመለከተ በጠ/ሚኒስትሩ እየተሰጠ ያለው ምዘና ከሞላ ጎዳል የሚያግባባ

ይመስለኛል። መሠረታዊ ልዩነት ሊኖር የሚችለው በችግሩ መሠረታዊ ምንጭ፣ በመፍትሔውና በፍጥነቱ ላይ ይሆናል ማለት ነው። ቀድም ሲል እንዳልኩት፣ "ስር ነቀለ ለውጥ" የሚሉ ሰዎች ለውጡ ከዚህም በበለጠ ፍጥነትና ጥልቀት እንዲካሔድ ሲጠይቁ፣ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ አፍርሶ መሥራት ቀርቶ መለወጥም ጭምር ለአገሪቱ አስቸጋሪ እንደሆነ የሚዘነጉት ይመስላል። ለውጡ በተቻለ ፍጥነት እንዲቀጥል መገፋፋት አስፈላጊ መሆኑን እቀበላለሁ። ሆኖም፣ “ስር ነቀል” ለውጥ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ከፖለቲካ ታሪካችን የሚመዘው መጥፎ ውርስ መሸከሙ ሳያንስ፣ አሁንም እንተግብረው ብንል አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል መዘንጋት አግባባ አይደለም እላለሁ።

አንድ ምሳሌ ላቅርብ። መከላከያው እና የጸጥታ ዘርፉ በፖለቲካ ገለልተኝነት ላይ በተመሠረት፣ ሞያዊ ብቃትን ባማከለ መንገድ መዋቀር እንዳለበት ሁላችንም እንስማማለን። “ስር ነቀል” ለውጥ የሚሉት ሰዎች፣ አሁን ባለንበት ፖለቲካዊ እውነታ አንጻር፣ ይህንን የመከላከያ እና የጸጥታ ዘርፍ አሁን እየተደረገ ካለው በተለየና በፈጠነ መንገድ መለወጥ ስለሚቻልበት አማራጭ ያቀረቡትን ዝርዝር አላየሁም። እነዚህን ከአናታቸው የተበላሹ የመከላከያ እና የጸጥታ መሥሪያ ቤት ተቋማት፣ በአነስተኛዋ ዋጋ ለመለውጥ ኢሕአዴግ ውስጥ ካለው የለውጥ ኃይል የተሻለ ተዋናይ አለን? ሠራዊትና የጸጥታ አካልን በአዋጅ በአንድ ምሽት አፍርሶ እንደ አዲስ ማቋቋም አይቻልም። አደገኛም ነው። ታዲያ፣ አገሩን ማን እየጠበቀው የዴሞክራሲ ሽግግር ሊደረግ ነው? የፍትሕ ሥርዓቱንም በዚሁ አመክንዮ መመልከት ይቻላል። የሕገ መንግሥት እና የፌዴራል አወቃቀሩን በተመለከተም ከዚህ የተለየ ግምገማ የለኝም።

ሐ፤ “የስር ነቀል” ለውጥ ክርክር ሌላው ማጠንጠኛ አገራዊ ተሐድሶውንም ሆነ ሽግግሩን በዋናነት ማን ይምራው ከሚለው ጥያቄ የሚመነጭ ነው። አንዱ ትችት “ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን ለኢሕአዴግ አደራ መስጠት ለአንበሳ ስጋ ጠብቅልኝ የማለት ያህል ነሆለልነት ነው” የሚል ነው። ተገቢና ችላ ሊባል የማይገባው ጥርጣሬ ነው። በኢሕአዴግ ውስጥ የተከናወነውን ለውጥ እና የአዲሱን ጠ/ሚ ፖለቲካዊ ቁመና ይሁነኝ ብሎ ከማሳነሱ ወይም ከትንተናው ለማስወጣት ከመሞከሩ በቀር ጥርጣሬውን እጋራለሁ። ብዙ የሽግግር ታሪኮች በገዢ ፓርቲዎች ቁልፍ ተዋናይነት መከናወናቸውን በምሳሌ ለማስታወስ አዳጋች ሆኖም አይመስለኝም። የዚህ ክርክር መነሻ ሦስት ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ። የመጀመሪያው ህወሓት/ኢሕአዴግ ለ27 ዓመታት የፈጸመው የውንብድና ተግባር እና ክህደቶች ያስከተሉት ጥልቅ ያለመተማመን መንፈስ ነው። ሁለተኛው፣ ሽግግሩን በአጋርነትም ቢሆን ሊመሩ የሚችሉ የሒደቱ አካል የሆኑ/የተደረጉ ተቋማት ወይም ስብስቦች አለመኖር ነው። ሦስተኛው፣ ጠ/ሚ ዐቢይ መንደርደሪያ የሚሆን ፍኖተ ካርታቸውን ቢያንስ መተማመንን ለማዳበር ሲባል አለማቅረባቸው ነው።

አገራዊ ተሐድሶውም ሆነ ሽግግሩ ከኢሕአዴግ ውጭ ያሉ አካላትም የሚሳተፉበት እንዲሆን መጠየቅና መታገል አስፈላጊ ነው። ይህን ለማድረግ ስር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋል መባሉ ላይ ልዩነት አለኝ። አገሪቱ አሁን ካለችበት ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የጸጥታ ውጥንቅጥ አንጻር፣ የስር ነቀል ለውጥ ጥሪ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ማሳሰብ አስፈላጊ ሆኖ ይሰማኛል። በተቃራኒውም፣ ጠ/ሚሩ የመረጡት መንገድ፣ የተመከረበት ፍኖተ ካርታ በሌለበት እርሳቸውንና ቡድናቸውን ብቻ አምነን እስከመጨረሻው እንደንደግፋቸው መጠየቅ ነው። ይህ ብዙ ርቀት የሚያስኬድ፣ አገራዊ ለውጥን መሸከም የሚችል ዘላቂ የትብብርና የመተማመን መንፈስ የሚያዳብር አካሔድ አይደለም። የስር ነቀል ለውጥ አማራጭን ዋጋም አላግባብ የሚያስወድድ ነው።

## መ፤ የሽግግር መንግሥት ወይም ብሔራዊ የአንድነት መንግሥት

አሁን ባለንበት ሁኔታ፣ ባወጣ ባወርደው አልገባህ ያለኝ መንገድ የሽግግር መንግሥት ምሥረታ የሚባለው ነው። ቢሆን ደስ የሚለኝ ሳይሆን ቀርቶ አይደለም። ነገሩ የማይሆን የሚመስለኝ በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ፣ ኢሕአዴግ ወደ ሽግግር (የአንድነት) መንግሥት ምሥረታ እንዲገባ የሚያደርግ የተደራጀ ገፊ ኀይል በሌለበት፣ ኢሕአዴግ ለምን ወደዚህ ምርጫ ይገባል? በኢሕአዴግ ውስጥ ያለው ሽኩቻና የኀይል አሰላለፍ ለዚህ ብጤው ሐሳብ አመቺ ነው? አይመስለኝም። ምናልባት ሕዝባዊ ግፊቱ እና ቀውሱ እንደገና ተቀስቅሶ ይህ ሁኔታ ካልተቀየረ በቀር፣ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ለጊዜው ሊሆን የሚችል አይመስለኝም።

የአሁኑን ለውጥ ያቀጣጠለው በከፊል የተደራጀ ሕዝባዊ ተቃውሞና አስፈሪ ፖለቲካዊ ቀውስ፣ የሽግግር መንግሥት መመሥረትን ግድ ወደሚያደርግበት ደረጃ ሳይደርስ “መመለሱ (መክሸፉ?)” የሚያከራክር አይደለም። አሁን እንደማደርገው በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ካልሆነ፣ ያቺ የግለት ነጥብ/መጠን በትክክል የት እንደምትገኝ ማወቅ አይቻልም።

ግለቱ በጥቂት ቢጨምር ውጤቱ ምን ሊሆን እንድሚችል በእርግጠኝነት ማወቅ አዳጋች ነው። ንቅናቄውና ቀውሱ ተመልሶ ይምጣ ቢባልም ምን እንደሚያስከትል አናውቅም። እንደ ኢትዮጵያ  ባሉ አገሮች እያንዳንዱ የለውጥ ንቅናቄ የመሻሻል እድል ብቻ ሳይሆን የቀውስ መአትም ሊያመጣ ይችላል።

የሽግግር መንግሥት ምስረታን ቢያንስ ለጊዜው የማይመስል የሚያደርገው ሁለተኛው ምክንያት፣ የዚህ መሰሉ መንግሥት አመሠራረት እና መስራቾች የሚሆኑት ኃይሎች/ቡድኖች ነጥረው ያልወጡ መሆናቸው ነው። የለውጥ ንቅናቄው በዋናነት ተቋማዊ ቅርጽ የያዘው በራሱ በኢሕአዴግ ውስጣዊ ቀውስ አቀጣጣይነት በመሆኑ፣ ከዚያ ውጭ ያሉት ቡድኖች ከሞላ ጎደል የዳር ተመልካቾች ናቸው። ተደራጅሁ ያለውን የፖለቲካ ቡድን ሁሉ የሚያካትት የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚለው የመፍትሔ ሐሳብ ሲናገሩት ከመቅለሱ በቀር ለንቋሳ መከራከሪያ ነው። እንደ አሸን የሚፈሉትን ሱቅ በደረቴዎች ሁሉ ሰብስቦ አገር መምራት የሚችል ጠንካራ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አይቻልም። ለሽግግር መንግሥቱ የተወሰኑት ይመረጡ ቢባል ደግሞ በተለይ ከብሔር ውክልና ጋራ በተያያዘ ሌላ የውዝግብ በር መከፈቱም አይቀርም። መከላከያው እና የጸጥታ አካላትም በዚህ መሰሉ የሽግግር መንግሥት ፖለቲካዊ እዝ ስር ለመሥራት ተቋማዊ አመላቸው አይፈቅድላቸውም።

ይሁን እንጂ፣ ቅርጹና ሥልጣኑ ቢለያይም፣ አገሪቱን ወደዴሞክራሲ ለማሸጋገር ኢሕአዴግ ከተቃዋሚዎችና ሲቪል ማኅበረሰቡ ጋራ በጋራ የሚሠራባቸው መድረኮችን መፍጠሩ ግዴታ እንደሆነ አሌ የሚባል አይደለም። ስለዚህ፣ የሽግግር ወይም ብሔራዊ የአንድነት መንግሥት የሚሉት ወገኖች፣ ድፍን ያለ ጥሪ ከማቅረብ ወጥተው ዘርዘር ያለ የአፈጻጸም አማራጫቸውን በጽሑፍ ለሕዝብ ማቅረብ አለባቸው። ሐሳባቸውን ለመደገፍም ሆነ ለመተቸት የሚቻለው ከድፍን ጥሪ ሲወጡ ብቻ ነው።

*ሠ፤ ቀጣዩ ምርጫ ወይስ መሥራች ምርጫ*

አሁን ያለንበትን የአገራዊ ተሐድሶ (ሪፎርም) ጅምር ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማሸጋገር ቀጣዩ የ2012 ምርጫ ቁልፍና አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን የሚገልጹ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሰዎች ሞልተዋል። ቀጣዩ ምርጫ ለዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ ህልውና "የሞትና የሽረት ጉዳይ" መሆኑን የሚገልጹ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ስመለከት በምርጫ ምትሃታዊ ኀይል ላይ ያላቸው እምነት ያስፈራኛል። ለዚህ ምርጫ የቀረን ከሁለት ዓመት ያነሰ ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችሉ ሕጋዊና ተቋማዊ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት፣ ውጤቱን በጸጋ ለመቀበል የሚያስችል ማኅበረሰባዊ መግባባት ለመፍጠር ይቻላልን? ሕግ ማርቀቅና ተቋማቱ ገለልተኛ እንዲሆኑ ማወጅ በሳምንታት ውስጥ ሊፈጸም የሚችል ሊሆን ይችላል። ሕጉና ተቋማቱ በተባለው መንገድ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ግን እንዲህ ቀላል አይሆንም። በብዛታቸው እና/ወይም በሌላ ማኅበረሰባዊ አቅማቸው አገራዊ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ ቡድኖች፣ የምርጫ ውጤቶችን እንዲቀበሉ የሚያደርግ መግባባት መፍጠርም በለብለብ የሚሠራ አይደለም።

ለቀጣዩ ምርጫ የቀረን ጊዜ ይህንን ለማስፈጸም በቂ ላይሆን ይችላል የሚለው ግምቴ፣ እስካሁን የመጣንበትን ሒደት ከመገምገም የሚነሣ ነው። ከዚህም በላይ ግን፣ "ምርጫ ወይም ቀውስ" የሚሉት ተቃዋሚዎች ከጋዜጣዊ መግለጫ የዘለለ፣ በመንግሥት ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚያስችል፣ ዝርዝር የይሁንታ ሐሳብ አለማቅረባቸው ያሳስባል። አሁንም ለመድገም፣ "ምርጫ ቦርድ ነጻና ገለልተኛ ይሁን" የሚል መግለጫ በቂ አይደለም። ከምርጫ ጋራ ተያይዞ ፖለቲካ ቀውስ ቢከሰት፣ የተጀመረው አገራዊ ተሐድሶ ይቀጥላል ወይስ ወደ ነበርንበት እንመለሳለን? ቀጣዩ ምርጫ የሞት የሽረት ጉዳይ ነው ከሚሉት አንዳንዶቹ፣ "ምርጫው ቀውስ ማስከተሉ ስለማይቀር ልንጠቀምበት እንችላለን" ብለው የሚያሰሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማሰብ ያስፈልጋል። ምርጫ የችግራችን ቁልፍ አይደለም።

ከዚህ በዘለለ ግን፣ ከግምት መግባት ያለበት ሌላው አማራጭ፣ ቀጣዩን ምርጫ እንደ ልዩ ምርጫ ቆጥሮ፣ ልዩ ዝግጅትና ድርድር ማድረግ ነው። ይህንን ምርጫ፣ "የሽግግር ምርጫ" ልንለው እንችላለን። በምርጫው አዲስ አገርም ይሁን ሥርዐት ባንፈጥር እንኳን፣ በክብደቱና በሚያስከትለው ውጤት ከቀደሙትም ይሁን ከሚመጡት የበለጠ ዋጋ እንዲኖረውና የአዲስ ምእራፍ መግቢያ እንዲሆን በማሰብ መዘጋጀት ይቻላል። ይህ ዝግጅትም ኢሕአዴ፣ ተቃዋሚዎች እና ሲቪል ማኅበረሰቡ በሚወከሉበት ስብስብ ሊመራ ይችላል።  የምርጫ ሕጉን ብቻ ሳይሆን ከምርጫ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ሕጎችና አሠራሮች ጭምር በመከለስ የሚጀምር ሊሆን ይችላል። ይህን መሰሉ ምርጫ፣ በፓርቲዎች መካከል ኮስተር ያለ ድርድር መደረጉን፣ መተማመን መፈጠሩን ግድ ይላል። በዚህ ስሜት ፓርቲዎቹ ከተስማሙ ቀጣዩ ምርጫ

ከመደበኛው ዘግይቶ ሊካሔድ ይችላል። ኢሕአዴግ እና ተቃዋሚዎች ለዚህ መሰሉ ድርድር ዝግጁ ናቸው? የአገራዊ ተሐድሶ/ሽግግር ፍኖተ ካርታዎች በሌሉበት ይህንን በእርግጠኝነት መመለስ አንችልም። ማን ምን እንደሚያስብም በግልጽ ማወቅ ቀላል አይሆንልንም።

በድጋሚ፣ መንግሥትን፣ ኢሕአዴግን እና ተቃዋሚዎችን ደጋግመን መጠየቅ ያለብን የየራሳቸውን ፍኖተ ካርታዎችን በተቻለ ፍጥነት ለአባሎቻቸውና ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርጉ ነው። ይህ በሌለበት የሚደመጥ ቅንጭብ ጥያቄና መግለጫ አንድ ጋት ወደፊት አያራምድም።

## እንደ መውጫ

አገራችን እያለፈችበት ያለውን ለውጥ ለመረዳት ተዋንያኑን እና የለውጡን ምእራፎች በየምኅዳራቸው ለያይቶ ማየት እንደሚያስፈልግ ለመጠቋቆም ሞክሬያለሁ። በኢሕአዴግ ውስጥ እየሆነ ያለውን፣ በመንግሥትና ከዚያም ውጭ ካለው አገራዊ ተሐድሶ ለይቶ መመልከት እጅግ አስፈላጊ ነው። ተዋናዮቹን በየምኅዳሮቻቸው መረዳትና መተንተን ካልቻልን፣ ድጋፋችንም ይሁን ትችታችን ብልቶቹን ከመላው አካል ለይቶ የሚያይ ካልሆነ፣ የዕለት ሁኔታውን ከዜና መዋዕሉ ካምታታነው ራሳችንን ለብስጭት ማዘጋጀት ይኖርብናል። በተመሳሳይ መልኩ፣ አገራዊ ተሐድሶውን እና ሽግግሩን በአነስተኛ ዋጋ ልናሳካ የምንችልባቸውን የመፍትሔ አማራጮች ስናሰላስል፣ የተለመዱት ሐሳቦች እስረኛ አለዚያም የሌሎችን የመገልበጥ ሱሰኛ እንዳንሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ የጀመሩት ተስፋ ሰጪ እርምጃ እንዲቀጥል ማበረታታት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አገራዊ የፖለቲካ ተሐድሶ እና ሽግግር ፍኖተ ካርታቸውን እንዲያሳውቁ መወትወት ይገባል። ተቃዋሚዎች እና ሲቪል ማኅበራትም በበኩላቸው የየራሳቸውን አማራጭ ፍኖተ ካርታዎች ለማዘጋጀት እንዲታትሩ መቀስቀስና መርዳት ያስፈልጋል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በርከት ያሉ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያሻቸው ወይም የተዘለሉ ወይም የተረሱ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ እገምታለሁ። መነበብን የሚከለክሉ ግን አይመስለኝም። ይህ ሁሉ ዳርዳርታ፣ በትችትም ይሁን በድጋፍ መልኩ፣ በዜናዎች ዙሪያ ከሚሽከረከር እሰጥ አገባ ወጥተን በዘላቂ ጭብጦች ላይ ወደመከራከር እንድንሸጋገር ለመጋበዝ ነው። ግብዣ ነው። ጥሪ ነው። ጠሪ አክባሪ!

በኢትዮጵያ ተስፋ አንቆርጥም። በጭራሽ!